# GLOBAL
# YOUTH CULTURE

## የኢትዮጵያ ሪፖርት





# ማውጫ

3 መግቢያ

5 ሐይማኖታዊ አመለካከቶች እና ባህሪያት
16 ተጽዕኖዎች እና መሪ ድምጾች
27 ግላዊ ልምዶች እና ተግዳሮቶች
39 ዲጂታል ግንኙነት እና ተፅዕኖ
51 የወደፊቱን መመልከት
57 ጾታዊ ማንነት

63 ስለ ዋንሆፕ
63 ስለ ጥናቱ

## እናመሰግናለን

በዚህ ፕሮጀክት ላይ ራዕዩን ለተካፈሉ እና ይህን ጥናት እውን ይሆን ዘንድ ላደረጉት አጋሮቻችን ልዩ ምስጋና እናቀርባለን። ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት (ኢወአሕ) ክልላዊ ጽ/ቤት እና ለታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት በኢትዮጵያ እውቅና ልንሰጥ እንወዳለን። መጪውን ትውልድ ለመረዳት እና በእግዚአብሔር ቃል ለመድረስ ስላላችሁ ቀና ልብ እናመሰግናለን።

# መግቢያ

እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን ልዩ ጥንካሬዎች እና ፈተናዎችን ይዞ ይመጣል ጥናት ደግሞ ዓለምን በትውልዱ አይን እንድንመለከት ያስችለናል፤ ይህም ፍላጎቶቻቸውን በተሻለ መንገድ እንድናሟላ ይረዳናል። የዛሬዎቹ ወጣቶችም ከዚህ የተለዩ አይደሉም።

ይህ ፕሮጀክት የኢትዮጵያ ወጣቶችን አመለካከት እና ህይወት በቅርበት በመመልከት በሀገሪቱ ውስብስብ ማህበራዊ ገጽታ መካከል ያላቸውንም  ልምድ ለመገንዘብ ይረዳል። በዚህ ጥናት፣ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ወጣቶች እምነቶች፣ ልማዶች፣ ተጽዕኖዎች እና በተጨማሪም ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ኢየሱስ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እና ስለ ቤተ ክርስቲያን ስላላቸው አመለካከት ጠለቅ ያለ ግንዛቤን እናገኛለን።



ከሐምሌ እስከ ጥቅምት 2024 ባለው ጊዜ ውስጥ ከገጠር፣ከተማ ቀመስ ከሆኑ አካባቢዎች እና ከከተሞች የተሰበሰበው ይህ መረጃ ቀጣዩን ትውልድ ለመቅረጽ ለሚደረጉ ሙከራዎች ብርሃንን ይፈነጥቃል። በጠቅላላ ሪፖርቱ ውስጥ አንዳንዶቹ ቁጥሮች 100% የማይሆኑት ከነጥብ በኋላ ያሉትን ቁጥሮች በማጠጋጋት ምክንያት ነው።

ይህ ፕሮጀክት የአፍሪካ ሃገራት የሆኑትን ኬንያን፣ ናይጄሪያን እንዲሁም ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ ከ20 በላይ ያሉ ሃገራት ወጣቶችን የዳሰሰ ትልቅ ዓለም አቀፋዊ ጥናት አካል ነው። የዚህ ዳሰሳ የተሻሻሉ ጥናቶች በ10 ተጨማሪ የአፍሪካ ሃገራትም ተካሂደዋል።

ተስፋችን ይህ ዘገባ አዳዲስ ግንዛቤዎችን የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን የወንጌልን ተስፋ የሚፈልገውን ይህን ትውልድ ወክላችሁ እርምጃ እንድትወስዱ እንዲያነሳሳችሁ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ስታስቲክስ ልዩ የሆነ ተስፋ፣ ፍራቻ እና ተግዳሮቶች ያሉትን እውነተኛውን ወጣት ይወክላል። እያንዳንዱ ወጣት ስም፣ ታሪክ እና የዘላለም እጣ ፈንታ አለው። ዋንሆፕ በአለም ዙሪያ ያሉ ወጣቶችን በእግዚአብሔር ቃል በመድረስ በእነዚያ እጣ ፈንታዎች ላይ ተጽእኖ ለማድረግ በቁርጠኝነት ይሰራል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚያካፍሉንን እናዳምጥ።

# ስለ ወጣቶች

## እድሜ

| 13-16 | 17-20 | 21-25 |
|---|---|---|
| 30% | 47% | 23% |

## ሃይማኖት[1]



የወንጌላውያን ክርስቲያን **62%**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን **29%**

ሙስሊም **7%**

ካቶሊክ **2%**

ሌላ ሐይማኖት **1%**[2]

**726በዳሰሳ ጥናቱ የተሳተፉ ወጣቶች**

ወንዶች **49%**

ሴቶች **51%**

## አካባቢ

**37%**
**ከተማ**
(50,000 ወይም ከዚያ በላይ)

**46%**
**ከተማ ቀመስ**
(በ2,500 እና በ50,000 መካከል)

**17%**
**ገጠር**
(ከ2,500 ያነሰ)

## ቤተሰብ



**45%** ሁለት ወላጆች

**22%** አንድ ወላጅ

**14%** ሌሎች የቤተሰብ አባላት

**19%** ሌላ የኑሮ ሁኔታ

---

1 የወንጌላውያን ክርስቲያኖች በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚይዙት ድርሻ በላይ በናሙናችን ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ—62% በመቶው ከ16% በመቶው ጋር ሲነጻጸር ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የመስክ ቡድኖች መረጃ የሰበሰቡበት ቦታ እና ያገኙበት መንገድ ነው። በዚህም ምክንያት ይህ ሪፖርት በተለይ በወንጌላውያን ወጣቶች ላይ ትኩረት ላደረጉ ስልቶች ጠቃሚ ይሆናል። የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ከአገራዊ አማካይ ሲነጻጸር 40% ሲሆኑ በእኛ ናሙና ግን (29%) ትንሹን ክፍል ይዘዋል፤ ቢሆንም በሪፖርቱ ውስጥ ለዚህ ቡድን ጠቃሚ የሆኑ ግንዛቤዎች አሉ።

2 ስድስት ወጣቶች ሌላ መርጠዋል። የእነርሱ ምላሽ: - አንድ አድቬንቲስት፣ አንድ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን እና አራት “ኢየሱስ ብቻ” ነበሩ። ለዚህ ሪፖርት፣ ከክርስቲያኖች ተነጥለው የተወሰዱ ሲሆን በጠቅላላው መዋዕቅራችን ውስጥ አልተካተቱም።

# ሃይማኖታዊ አመለካከቶች እና ባህሪያት

የኢትዮጵያ ሪፖርት

# ያገኘነው

**ከ10 ምላሽ ሰጪዎች 9ኙ**
**ጥናት ደግሞ** አስፈላጊ አካል እንደሆነ ተናግረዋል።



ጥናቱ ከተካሄደባቸው ወጣቶች መካከል **93%** **ክርስቲያን** ናቸው።



**አንድ ሶስተኛ** ከሚሆኑት ወጣቶች መካከል ብዙ ጊዜ **መንፈሳዊ ውይይቶችን** ከሌሎች እምነታቸውን ከማይጋሩ ሰዎች ጋር እንደሚያደርጉ ይናገራሉ።



**53%** የሚሆኑት ወጣት ክርስቲያኖች **የተሰጡ ክርስቲያኖችን** እምነት እና ባህሪ ያሳያሉ።



**ክርስቲያን ወጣቶች** በአጠቃላይ **የታተመውን** መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብን ይመርጣሉ፣ ጥቂቶች መተግበሪያውን መጠቀም ይወዳሉ።

# ሃይማኖታዊ አመለካከቶች እና ባህሪያት

ይህ የዳሰሳ ጥናት እምነት እና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ወጣቶች ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ሚና በተለየ መንገድ አጠቃልሎ የፈተሸ ነበር። የሚያምኑት ምንድነው? እምነታቸውን በተግባር የሚያውሉት እንዴት ነው? የዚህ ትውልድ ሃይማኖታዊ አመለካከቶች እና ባህሪያት በሌሎች የሕይወታቸው ክፍሎች ውስጥ ያለውን ተጽዕኖ መርምረናል።

በጥናታችን ውስጥ አብዛኛዎቹ ወጣቶች እራሳቸውን የወንጌላዊያን ወይም የኦርቶዶክስ ክርስቲያን (91%) መሆናቸውን ሲገልጹ ቀሪዎቹ ድግሞ ሙስሊም ወይም ሌላ ሃይማኖት ይከተላሉ። እነዚህ ምድቦች የሃገሪቱን ሃይማኖታዊ ገጽታ የሚያንፀባርቁ ናቸው፣ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እና ሙስሊም ወጣቶች በአጠቃላይ እዚህ ከሚንፀባረቁበት የበለጠ ብዙ ቢሆኑም።[1] የወንጌላውያን እና ሙስሊም ምላሽ ሰጪዎች በብዛት ከተማ ቀመስ ከሆኑ አካባቢዎች እና ከከተሞች ናቸው። የኦርቶዶክስ ምላሽ ሰጪዎች ደግሞ ሁለቱንም የገጠር እና የከተማውን አካባቢ የበለጠ ይወክላሉ።

## ዋና ሃይማኖታዊ ማንነቶች ውይይት ተደርጎባቸዋል[2]




## ሐይማኖት በአካባቢ




1 የ2020 የዓለም ሃይማኖት መረጃ፤ ሀገራዊ የሐይማኖት ስርጭቱን ሲተነትን 40% የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣34% የሱኒ ሙስሊም እና 16% ፕሮቴስታንት ክርስትያን እንደሆነ ግምቱን አስቀምጧል። https://www.thearda.com/world-religion/national-profiles?u=78c

2 የናሙናችን 3% የሚሆኑት የካቶሊክ እና የሌሎች ሃይማኖቶች ሲሆኑ በጠቅላላ ሪፖርቱ ውስጥ ለማካተት በጣም ትንሽ ናቸው።

ጥናቱ የተካሄደባቸው አብዛኞቹ ወጣቶች ሃይማኖታቸው ለእነሱ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ። 90 በመቶው ሐይማኖታዊ እምነታቸው ወይም መንፈሳዊ ጉዟቸው የማንነታቸው አስፈላጊ አካል ነው ይላሉ። ይህ በተለይ ለወንጌላውያን ክርስቲያኖች እውነት ነው።

> **90%** የሚሆኑት ወጣቶች እምነታቸው ለእነርሱ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ።

## እምነት በሃይማኖት ውስጥ ያለው አስፈላጊነት

**የእምነት አመለካከቶቼ ወይም መንፈሳዊ ጉዞዬ የእኔ ማንነት አስፈላጊ አካል ናቸው።**




# መሰጠት

እምነት በወጣቶች ሕይወት ውስጥ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት እንዴት ማወቅ እንችላለን? ሃይማኖት ለእነሱ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የሙሉ ማንነታቸው እና ንፅረት ዓለማቸው እይታ አካል እንደሆነ ምን ጠቋሚዎች ያሳዩናል? አንድ ወጣት የተሰጠ ክርስቲያን መሆኑን የሚያሳዩ አንዳንድ መሠረታዊ እምነቶችን እና ቁልፍ መንፈሳዊ ተግባራት ተመልክተናል።

## 6 የተሰጡ ክርስቲያኖች ባህሪያት



- እግዚአብሔር እንዳለ እና በግል ከእርሱ ጋር ግኑኝነት ሊኖራቸው እንደሚችል ያምናሉ
- ቢያንስ በየሳምንቱ ይጸልያሉ
- ቢያንስ በየሳምንቱ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳቸው ያነብባሉ
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያምናሉ
- የኃጢአት ይቅርታ ሊገኝ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሆነ ያምናሉ
- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያምናሉ

በዚህ የተሰጠ እምነት ፍቺ መሰረት ወጣቶችን ደግመን ስንመረምር ትልቅ ልዩነት አይተናል። 53 በመቶ የሚሆኑት ክርስቲያን ወጣቶች የተሰጡ ክርስቲያኖች መሆናቸው ታውቋል። በዚህ ጥናት ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን የተሰጠ ክርስቲያን መስፈርቶችን ያላሟላ ማንኛውም ክርስቲያን ወጣት እንደ “የስም ክርስቲያን” ይቆጠራል።




53%በዳሰሳ ጥናቱ የተመለከትናቸው ክርስቲያኖች የተሰጡ ናቸው።

በዳሰሳ ጥናቱ ከተመለከትናቸው ክርስቲያኖች መካከል ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ይበልጥ የተሰጡ ናቸው። ወንጌላውያን ደግሞ ከኦርቶዶክስ ይልቅ የተሰጡ የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው።

## መሰጠት በጾታ



## መሰጠት በሃይማኖት







በዚህ የዳሰሳ ጥናት የተሰጡ ክርስቲያኖች በመቶኛ ከብዙ ቀደምት Global Youth Culture (GYC) ጥናቶች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነበር። በአለም አቀፍ ደረጃ፣ በመጀመሪያው GYC ጥናታችን ውስጥ 7% የሚሆኑት ወጣቶች የተሰጡ ክርስቲያኖች መሆናቸውን አረጋግጠዋል።[1] ጥናቱ በተካሄደባቸው የአፍሪካ ሃገራት ይህ አሃዝ ወደ 28% ከፍ ብሏል—ከሁሉም ክልሎች ከፍተኛው ነው።[2] በኡጋንዳ በ2023 GYC ፕሮጄክታችን ጥናቱ ከተካሄደባቸው ታዳጊ ወጣቶች መካከል 33% የሚሆኑት የተሰጡ ክርስቲያኖች መሆናቸው ታውቋል። በዚህ ዐውድ፣ ጥናቱ በተደረገባቸው ክርስቲያኖች መካከል 53% የሆኑት የተሰጡ መሆናቸው በጣም ተስፋ ሰጭ ነው።

# መንፈሳዊ አይታዎች

አብዛኞቹ ጥናቱ የተደረገባቸው የወንጌላውያን ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር፣ ኢየሱስ እና መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ አሏቸው። የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በመሰረታዊ አስተምህሮ በአብዛኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው ነገር ግን ከወንጌላውያን አንጻር የተወሰነ ልዩነት ይታይባቸዋል። ሙስሊሞች በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት መኖር እንደሚገባው ይስማሙ እንጂ፤ ስለ ኢየሱስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና የኃጢአት ይቅርታ የሰጡት ምላሽ ከክርስቲያኖች ቀኖና አንጻር ፍጹም የተለየ ቢሆንም ግን የሚያበረታታ ምላሽ ነው።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከቶች በሐይማኖት

| | ወንጌላውያን | ኦርቶዶክስ | ሙስሊም |
|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር አለ እና ከእርሱ ጋር ግላዊ ግንኙነት ሊኖረኝ ይችላል። | 94% | 80% | 70% |
| ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። | 96% | 87% | 31% |
| መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። | 96% | 87% | 41% |
| የኃጢአት ይቅርታ ሊገኝ የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው። | 94% | 87% | 26% |

1 OneHope. (August 2020). Global Youth Culture, Global Report. www.globalyouthculture.net
2 በመጀመሪያው የ2020 ጥናት ሦስቱ የአፍሪካ አገሮች ኬንያ፣ ናይጄሪያ እና ደቡብ አፍሪካ ነበሩ።

# ወጣቶች እምነታቸውን እንዴት ይለማመዳሉ

እምነቶች በእርግጠኝነት አስፈላጊ ናቸው፣ ነገር ግን በመንፈሳዊ ስርአቶች ውስጥ መሳተፍ ደግሞ እምነታችንን የምናሳድግበት መንገድ ነው። ጥናቱ የተካሄደባቸው አብዛኞቹ ወጣቶች በሳምንታዊ መርሃ ግብራቸው ውስጥ ለሐይማኖታዊ ልምምዶቻቸው ቅድሚያ እየሰጡ መሆናቸውን በመመልከታችን ተበረታተናል።

ከ4ቱ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች 3ቱ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ሃይማኖታዊ ቅዱሳት መጻሕፍትን (ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን ወይም ቁርኣንን) ያነባሉ። ጸሎት ይበልጥ የተለመደ ነው፣ 84% የሚሆኑት በየሳምንቱ ይጸልያሉ። በሐይማኖታዊ አገልግሎቶች ላይ መሳተፍ (80%) በስፋት የሚደረግ ነው። አነስተኛው—ከ3ቱ 1 የሚሆኑት—በየሳምንቱ እምነታቸውን እንደሚያካፍሉ ይናገራሉ። እምነታቸውን በቀጥታ ለሌሎች ማካፈል ከሌሎች ሃይማኖታዊ ልምምዶች ባነሰ ሁኔታ የሚከሰት ቢሆንም፣ አንድ ሶስተኛው በየሳምንቱ ማድረጉ ትርጉም ያለው ነው።

## የእምነት ልምምዶች






# በክርስቲያኖች መካከል ያለ መንፈሳዊ ተግባራት

እነዚህ ልማዶች በተለይ በክርስቲያኖች ዘንድ ምን እንደሚመስሉ ለማየት እንፈልጋለን። ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ከኦርቶዶክስ አቻዎቻቸው ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ እድላቸው ከፍተኛ ነው። እንዲሁም ቤተክርስቲያን የመገኘት፣ የመጸለይ እና እምነታቸውን ለሌሎች የማካፈልን በከፍተኛ መጠን ሪፖርት አድርገዋል። የተሰጡ ክርስቲያኖች በአራቱም ምድቦች ከፍተኛውን ደረጃ አስመዝግበዋል።

## መንፈሳዊ ተግባራት

| | ወንጌላውያን | ኦርቶዶክስ | ሁሉም ክርስቲያኖች |
|---|---|---|---|
| **የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ**<br>ቢያንስ በየሳምንቱ መጽሐፍ ቅዱስን አነባለሁ | 82% | 53% | 73% |
| **ጸሎት**<br>ቢያንስ በየሳምንቱ እጸልያለሁ | 89% | 74% | 84% |
| **ቤተክርስቲያን በቋሚነት መገኘት**<br>ቢያንስ በየሳምንቱ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ | 86% | 65% | 79% |
| **እምነታቸውን ለሌሎች ማካፈል**<br>ስለ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ነገሮች ቢያንስ በየሳምንቱ እምነቴን ከማይጋሩ ሰዎች ጋር እወያያለሁ | 38% | 26% | 34% |

| | የተሰጡ ክርስቲያኖች | የስም ክርስቲያኖች |
|---|---|---|
| **መጽሃፍ ቅዱስን ማንበብ**<br>ቢያንስ በየሳምንቱ መጽሐፍ ቅዱስን አነባለሁ | 100% | 43% |
| **ቤተክርስቲያን በቋሚነት መገኘት**<br>ቢያንስ በየሳምንቱ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ | 93% | 65% |
| **ጸሎት**<br>ቢያንስ በየሳምንቱ እጸልያለሁ | 100% | 66% |
| **እምነታቸውን ለሌሎች ማካፈል**<br>ስለ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ነገሮች ቢያንስ በየሳምንቱ እምነቴን ከማይጋሩ ሰዎች ጋር እወያያለሁ | 41% | 27% |

የእለት ተእለት ልምምድን ስንመለከት፣ በተሰጡ እና በስም ክርስቲያኖች መካከል እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እና መጸለይ ባሉ ዋና መንፈሳዊ ተግባራት ላይ ባላቸው ልምምድ ውስጥ ያለውን ክፍተት እናያለን። ያም ሆኖ ከ 4 የስም ክርስቲያኖች 1 የሚሆነው መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ ማንበቡ የሚያበረታታ ነው።

## ዕለታዊ መንፈሳዊ ተግባራት




# ወጣት እና መጽሐፍ ቅዱስ

በዳሰሳ ጥናቱ ከተካፈሉት ክርስቲያን ወጣቶች አብዛኞቹ መጽሐፍ ቅዱስን ቢያንስ በየሳምንቱ ያነብባሉ (73%)። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ክርስቲያን ወጣቶች የታተመውን መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያነቡ የተናገሩ ሲሆን። ከ4ቱ አንዱ ደግሞ በመተግበሪያ እንደሚያነቡ ተናግረዋል።

ጥቅም ላይ የዋሉት የመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረቦች እንደ ሃይማኖቱ እና እንደ አካባቢው በተወሰነ መልኩ ይለያያሉ። ወንጌላውያን አማኞች ከኦርቶዶክስ አማኞች ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን በመተግበሪያ እንዳነበቡ ለመናገር ሰፊ እድል አላቸው። የገጠር ምላሽ ሰጭዎች ብዙ ጊዜ ህትመቶችን ሲጠቀሙ ከ3 የከተማ ወጣቶች አንዱ መተግበሪያውን እንደሚጠቀሙ ተናግረዋል።

## የመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ

መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ታነባላችሁ? (የሚመለከተውን ሁሉ ምረጡ)



## በክርስቲያኖች መካከል ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ

መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ያነባሉ? (የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ)




## የመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ በአካባቢ

መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ታነባላችሁ? (በድምጽ እና ድረ ገጽ ሳይጨምር)



# ማጠቃለያ

ይህ መረጃ ወጣቶች በመንፈሳዊ ጉዟቸው የት እንዳሉ ያሳያል እና ሃይማኖታዊ ማንነታቸውን፣ ልማዶቻቸውን እና አመለካከታቸውን እንድንረዳ ይረዳናል። ይህ በተጨማሪም ለማያምኑ ወጣቶች ወንጌልን ለመንገር እና እና በእምነት ያልጠነከሩ ወጣቶችን ደቀ መዝሙር ለማድረግ መውሰድ የሚገባንን ተግባራዊ እርምጃን ይጠቁመናል።

- **ክርስቲያኖችን ለጠለቀ እምነት ደቀመዝሙር ማድረግ**
  በጥናቱ የተሳተፉ ወጣቶች እምነታቸው ለእነርሱ አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል። ይህ በተለይ በወንጌላውያን ክርስቲያኖች ዘንድ እውነት ነው። ይህ ማለት ግን ቤተክርስቲያን በዚህ ረክታ መቀመጥ አለባት ማለት አይደለም። ብዙ አማኞች የላይ ላይ እምነት እንዳላቸው እና ቀጣይነት ያለው ደቀመዝሙርነት እንደሚያስፈልጋቸው ጥናታችን አረጋግጧል። ወጣቶች በጥልቀት እምነታቸውን እንዲያውቁ የመሞገት አስፈላጊነት በተለይ ከወንጌላውያን ክርስቲያኖች ያነሰ መሰጠት ላላቸው ለወጣት ኦርቶዶክሳውያን አማኞች አስፈላጊ ነው።

  ወጣቶች የስም አማኞች ከመሆን ይልቅ የበሰሉ፤ ያደጉ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ የሚረዷቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነቶችና መንፈሳዊ ተግባሮች እንዲያዳብሩ መርዳት የምንችለው እንዴት ነው?

- **ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ማጠናከር**
  በወጣቶች ህይወት ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያላቸው ግኑኝነት ሊጠናከር ይችላል። ግኑኝነታቸውን ለማዳበር የሚያስችል መንገድ መኖሩ መልካም ዜና ነው። በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ማንበብ ልምድ ስንመጣ፣ 60% የሚሆኑት የተሰጡ ክርስቲያኖች እና 24% የሚሆኑት የስም ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በየቀኑ እንደሚያነቡ ተናግረዋል። እነዚህ ቁጥሮችበተለይም ከወንጌላውያን አቻዎቻቸው ላነሰ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በሚያነቡት በኦርቶዶክስ አማኞች መካከል አድገው ማየት እንወዳለን።

  የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታቸው ውስጥ በሚያጋጥሟቸው እውነተኛ ፍላጎቶችና ፈታኝ ሁኔታዎች እንዲናገራቸው መፍቀድ እንዲችሉ ወጣቶች በሕይወታቸው ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ማጠናከር የምንችለው እንዴት ነው?

- **ወጣቶች እምነታቸውን እንዲያካፍሉ ማስታጠቅ**
  በጥናቱ የተካፈሉ ወጣቶች በሙሉ ማለት ይቻላል እምነታቸው የሕይወታቸው አስፈላጊ አካል እንደሆነ ተናግረዋል። ነገር ግን፣ ከነዚህ ወጣቶች መካከል አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት ብቻ ስለ ሃይማኖታዊ እምነታቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር ይነጋገራሉ። ከተሰጡት ክርስቲያኖች መካከል እንኳ እምነታቸውን አዘውትረው ለሌሎች እንደሚያካፍሉ የተናገሩት ከግማሽ ያነሱ ናቸው። እምነታችንን ሙሉ በሙሉ መኖር ጥበባችንን፣ልምዳችንን እና እምነታችንን ለሌሎች ማካፈልን ይጨምራል።

  ወጣቶች በክርስቶስ ያላቸውን ተስፋ ከጓደኞቻቸው እና ለሌሎች መስማት ለሚያስፈልጋቸው በማህበረሰባቸው ላሉ ሰዎች በደስታ እንዲያካፍሉ እንዴት እናስታጥቃቸው?

- **ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ለማሻሻል የዲጂታል አማራጭ መፍጠር**
  አብዛኛዎቹ ምላሽ ሰጪዎች የታተመውን መጽሐፍ ቅዱስ ያነባሉ፣ ነገር ግን ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ መተግበሪያዎችን ይጠቀማሉ፣ በተለይም በወንጌላውያን ዘንድ 35% መተግበሪያውን እንደሚጠቀሙ ሪፖርት በማድረጋቸው ይህ እየተለመደ መሆኑን ማሳያ ነው። የስማርትፎን ባለቤት የሆኑ ወጣቶች ቁጥራቸው እየጨመረ ስለሚመጣ የመጽሕፍ ቅዱስ ዲጂታል ተደራሽነት በሚቀጥሉት ዓመታት ሊሰፋ ይችላል። ይህ ለውጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለን ግኑኝነት ለማዳበር፣ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን በቀላሉ ለማግኘት እና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ጥልቅ ግንኙነት እንዲኖረን የሚያበረታቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ወይም የአምልኮ መመሪያዎችን ለማቅረብ አስደሳች እድሎችን ይከፍታል።

  እያደገ የመጣውን የኢትዮጵያን ዲጂታል አሻራ የወንጌልን ተደራሽነት ለማስፋት እና ጥልቅት እንዲኖረው ለማድረግ እንዴት መጠቀም እንችላለን?

# ተጽዕኖዎች እና መሪ ድምጾች

የኢትዮጵያ ሪፖርት

# ያገኘነው

**ወጣቶች** በእነሱ ላይ **ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳርፉት ወላጆቻቸው ስለሆኑ ምክር ሲፈልጉ** ወደ እነርሱ እንደሚሄዱ **ተናግረዋል።**



ወጣቶች እያደጉ ሲሄዱ የወላጆች ተጽእኖ ሲቀንስ **የሃይማኖት መሪዎች እና የጽሑፎች ተጽዕኖ እያደገ ይሄዳል።**

**76%** የሚሆኑ ወጣቶች **በደንብ የሚያውቋቸው የቅርብ ጓደኞች አሏቸው።**



**የቅርብ ጓደኝነት** በገጠር አካባቢዎች ብዙም የተለመደ አይደለም።



**ስለ** ሥርዓተ-ፆታ እና ወሲባዊ ጉዳዮች የምክር እና የምሪት ምንጭ **ሆነው በከፍተኛ ሁኔታ ሪፖርት የተደረጉት ጓደኞች** ሲሆኑ **ቤተሰብ፣ የኃይማኖት አባቶች እና በጉዳዩ ላይ የተጻፉ ጽሁፎች በሪፖርቱ ውስጥ ቀጣዮቹን** ከፍተኛ ደረጃዎች ይዘዋል።

# የቤተሰብ ግንኙነቶች

ለሕይወት ያላቸው ዓላማ እና ጉጉት ላይ ተጽዕኖ ያሳደረባቸው ማን እንደሆነ ወጣቶችን ስንጠይቅ፣ ወላጆችን የጠቀሱት በጣም ጥቂቶቹ ነበሩ። ጓደኞች አርአያ ሆነውናል ብለው ደጋግመው ጠቅሰዋቸዋል። ምናልባትም እንደሚጠበቀው በዚህ በወጣትነት ዕድሜ የወላጆች ተጽእኖ እየቀነሰ  የሚመጣ ቢሆንም ያን ያህል ግን አልቀነሰም። የሙስሊሞች ምላሽ ሰጪዎች ከሌሎች የሐይማኖት ተከታይ ወጣቶች ይልቅ ጓደኞቻቸውን የመምረጥ እድላቸው ከፍተኛ ነበር።

## በፍላጎት ላይ ያሉ ተጽእኖዎች

ለህይወት ባላችሁ ጉጉት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው ማነው? (የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ)




## በህይወት ጉጉት እና ምኞት ላይ የወላጆች ተጽዕኖ በእድሜ



# በህይወት ጉጉት እና ምኞት ላይ ሶስት ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በሃይማኖት




ስለወጣቶች ቤተሰባዊ ግንኙነት እና አኗኗር የበለጠ ለማወቅ እንፈልጋለን። በኢትዮጵያ በጥናቱ ከተካፈሉ ወጣቶች መካከል አርባ-አምስት በመቶው ከሁለቱም ወላጆች ጋር ይኖራሉ። በገጠር ወጣቶች መካከል አሉታዊ የቤተሰብ ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ ከፍ ያለ እና በኦርቶዶክስ ወጣቶች ዘንድ ደግሞ ይበልጥ የተለመደ ነበር።

**79%** ወጣቶች ከቤተሰባቸው ጋር እንደሚኖሩ ተናግረዋል ግኑኝነታቸውም ጥሩ ነበር።

# ቤተሰብ

አብሬ የምኖረው:-



## የቤተሰብ ግንኙነቶች በአካባቢ

በአጠቃላይ ከቤተሰቤ ጋር ያለኝ ግንኙነት ጥሩ ነበር።




## የቤተሰብ ግንኙነቶች በሃይማኖት

በአጠቃላይ ከቤተሰቤ ጋር ያለኝ ግንኙነት ጥሩ ነበር።




የቤተሰብ ውይይቶች የመቀራረብ እና የመተሳሰብ ምልክት ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኞቹ ወጣቶች ቢያንስ አንዳንድ ጊዜ ከወላጆቻቸው ጋር ለእነሱ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ ጉዳዮች እንደሚነጋገሩ ይናገራሉ። እነዚህን አስፈላጊ ንግግሮች ብዙ ጊዜ ለማድረግ የተሰጡ ክርስቲያኖች ከስም ክርስቲያኖች የበለጡ ናቸው። ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ከወላጆቻቸው ጋር ብዙ ጊዜ የመነጋገር እድላቸው ሰፊ ነው።

## ከወላጅ ጋር የሚደረጉ ውይይቶች

ለእኔ ዋጋ ስላላቸው ነገሮች ከወላጆቼ/ከአሳዳጊዎቼ ጋር አወራለሁ።









# ወጣቶች ቤተሰብን ያምናሉ

ወጣቶች ስለ ሕይወት ትርጉም ሲያስቡ ከማንኛውም ሌላ ምንጭ በበለጠ ወደ ቤተሰብ እና የሃይማኖት መሪዎች ወይም ጽሑፎች እንደሚዞሩ ይነግሩናል። ትክክልና ስህተት የሆነውን ነገር ለመለየት ለሚጠይቁ ወጣቶች ዋነኛ የመረጃ ምንጭ የሆኑት መጀመሪያ የቤተሰብ አባላት ቀጥሎ የሃይማኖት ጽሁፎች ናቸው። ጓደኞች ወይም እኩዮች ለሁለቱም ምድቦች ሦስተኛ እና በጣም የተለመዱ ምርጫዎች ናቸው።

## ስለሕይወት ትርጉም ውይይቶች

ስለ ሕይወት ትርጉም መረጃ ወይም መመሪያ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምሄደው፡-

1. የቤተሰብ አባላት **33%**
2. የሐይማኖት መሪዎች/ጽሁፎች **33%**
3. ጓደኞች/እኩዮች **19%**
4. ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ኢንተርኔት **8%**
5. አስተማሪዎች/አማካሪዎች **4%**
6. ከኢንተርኔት ውጪ የሆነ ሚዲያ[1] **3%**

## ስለትክክል እና ስህተት ውይይቶች

ስለ ሕይወት ትርጉም መረጃ ወይም መመሪያ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምሄደው፡-

1. የቤተሰብ አባላት **34%**
2. የሐይማኖት መሪዎች/ጽሁፎች **25%**
3. ጓደኞች/እኩዮች **19%**
4. ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ኢንተርኔት **10%**
5. አስተማሪዎች/አማካሪዎች **8%**
6. ከኢንተርኔት ውጪ የሆነ ሚዲያ **4%**

1 ከኢንተርኔት ውጭ ያለ ሚዲያ መጽሃፎችን፣ መጽሔቶችን፣ ቴሌቪዥንን፣ ሬዲዮን ወይም ጋዜጣን ያጠቃልላል።

ዕድሜ እና ሐይማኖት ሁለቱም ወጣቶች የማንን ምክር ይፈልጋሉ በሚለው ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ። እያደጉ ሲሄዱ፣ ወጣቶች መመሪያ ለማግኘት ወደ ቤተሰባቸው መሄዳቸው እየቀነሰ ሲሄድ፣ የሃይማኖት መሪዎች ወይም ጽሑፎች ደግሞ ተጽዕኗቸው እየጨመረ ይሄዳል። ከሃይማኖት ተቋማት መካከል፣ በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ምክር ለማግኘት ወደ ሃይማኖት መሪዎች ወይም ጽሑፎች በመዞር ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በብዛት ይገኛሉ።

## ከፍተኛዎቹ ሁለቱ ተጽኖዎች በዕድሜ

ስለ ሕይወት ትርጉም መረጃ ወይም መመሪያ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምሄድበት፦




ትክክል እና ስህተት ስለሆነው ነገር መረጃ ወይም መመሪያ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምሄድበት፦




## ሁለቱ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በሃይማኖት

ስለ ሕይወት ትርጉም መረጃ ወይም መመሪያ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምሄድበት፦




ስለ ሕይወት ትርጉም መረጃ ወይም መመሪያ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምሄደው፦



# ለሥርዓተ-ፆታ ጥያቄዎች ጓደኞች ቁልፍ ናቸው

ወጣቶች ስለ ስርዓተ ጾታ እና ወሲብነክ የመሳሰሉት ውስብስብ ርዕሰ ጉዳዮች መመሪያ ለማግኘት ወደ የት እንደሚሄዱ እንዲነግሩን ጠይቀናል። ወጣቶች ስለእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች መመሪያ ለማግኘት አብዛኛውን ጊዜ መጀመሪያ ጓደኞቻቸውን ከዚያም ቤተሰብ እና የሃይማኖት መሪዎች ወይም ጽሑፎች እንደሚፈልጉ ይናገራሉ።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ወጣቶች በኢንተርኔት አማካኝነት ምክር ከመጠየቅ ይልቅ መመሪያን ከሚተማመኑበት ሰው ጋር ባላቸው ግኑኝነት ለማግኘት ይመርጣሉ። ይሁን እንጂ 13 % የግል ስልክ የሌላቸውን ወጣቶች ጨምሮ ወደ ማህበራዊ ሚዲያው ዞር ማለታቸውን ሪፖርት አድርገዋል። ምንም እንኳን ወጣቶች ምሪትን ፍለጋ ከሚሄዱባቸው መጀመሪያዎቹ ሶስት ቦታዎች መካከል ቢሆኑም  ቤተሰብ እና የኃይማኖት መሪዎች ከሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ይልቅ በዚህ ረገድ ያላቸው ተጽዕኖ አነስተኛ እንደሆነ አስተውለናል።

**ተጽእኖዎች በ**
**የሥርዓተ ጾታ አመለካከቶች**

ስለ ሥርዓተ ጾታ፣ ጾታ እና ወሲብ ነክ ጉዳዮች መረጃ ወይም መመሪያ ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምሄደው፡-

1. ጓደኞች/እኩዮች **30%**
2. የቤተሰብ አባላት **23%**
3. የሃይማኖት መሪዎች ወይም ጽሑፎች **18%**
4. ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ኢንተርኔት **13%**
5. አስተማሪዎች/አማካሪዎች **12%**
6. ከኢንተርኔት ውጪ የሆነ ሚዲያ[1] **4%**

1 ከኢንተርኔት ውጭ ያለ ሚዲያ መጽሃፎችን፣ መጽሔቶችን፣ ቴሌቪዥንን፣ ሬዲዮን ወይም ጋዜጣን ያጠቃልላል።

ሴቶች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ቤተሰብን የማማከር እድላቸው ከወንዶች በእጥፍ ይበልጣል። ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ከሌሎች የሃይማኖት ተቋማት ይልቅ ወደ ቤተሰብ አባላት እና የሃይማኖት መሪዎች ወይም ጽሑፎች ይሄዳሉ። የተሰጡ ክርስቲያኖች ከስም ክርስቲያኖች ይልቅ በቤተሰብ ወይም በሃይማኖት ምንጮች የመታመን እድላቸው ሰፊ ነው።

## በሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ላይ ዋናዎቹ ሶስት ተጽእኖዎች በፆታ




## ስለስርዓተ ጾታ ባለ አመለካከት ላይ ያሉ ተጽእኖዎች በሃይማኖት



## በሥርዓተ-ፆታ አመለካከት ላይ ዋናዎቹ ሶስት ተጽእኖዎች በመሰጠት




# ጓደኝነት እና ማህበረሰብ

በሚያበረታታ ሁኔታ፣ በጥናቱ የተካፈሉት አብዛኞቹ ወጣቶች (76%) በሕይወታቸው ውስጥ ጠንካራ ጓደኝነት እንዳላቸው ተናግረዋል። የገጠር አካባቢዎች የቅርብ ጓደኞች እንደሌላቸው ሪፖርት የማድረግ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። በእድሜ፣ በፆታ ወይም በሃይማኖት ምንም ጉልህ የሆኑ ልዩነቶች የሉም።

## ጓደኝነት

በደንብ የሚያውቁኝ የቅርብ ጓደኞች አሉኝ።




## ጓደኝነት በአካባቢ



# ማጠቃለያ

የዛሬዎቹ ወጣቶች የህይወት ውስብስብ ጉዳዮችን እና ጥያቄዎችን ሲዳስሱ፣ የሚያዳምጧቸው ድምፆች ወሳኝ ናቸው። ወጣቶች የሚያምኗቸው እና በሚያምኑት ነገር ላይ ግንዛቤን ለማዳበር የሚሄዱባቸው ምንጮች? እናም በጥልቀት የሚያምኑት በአኗኗራቸው እና በድርጊታቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

- **ቤተሰብ ወሳኝ ሚና አለው**
  በሚያበረታታ ሁኔታ፣ ወጣቶች ወላጆቻቸው በሕይወታቸው ውስጥ ቀዳሚ ተጽእኖ እንዳላቸው እና የቤተሰብ አባሎቻቸውን ለሕይወት በጣም አስፈላጊ ለሆኑ ጥያቄዎች መሪ አድርገው እንደሚያምኑ ተናግረዋል። ወላጆች በልጆቻቸው ሕይወት ላይ በተለይም በወጣትነታቸው እና ለመስማት በጣም ዝግጁ በሆኑ ወቅት ተሰሚ እንዲሆኑ የተሰጣቸውን እድል በቀላሉ ሊያዩት አይገባም።

  > ወላጆች ህጻናት እና ወጣት ልጆቻቸውን የመገሰጽ እና በስነስርዓት የማሳደግ ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱ እንዴት ማብቃት እንችላለን?

- **መጽሐፍ ቅዱስን መመሪያችሁ መሆኑን አረጋግጡ**
  ወጣቶች ለሀይማኖት መሪዎች እና ጽሑፎች ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ፣ ከቤተሰቦቻቸው ቀጥሎም በእነሱ ላይ ቁልፍ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፉባቸው ይናገራሉ። ይህ በክርስቲያን ወጣቶች ሪፖርት እንደተደረገው የሳምንታዊ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ጎልቶ ይታያል። ወጣቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ የሆነውን ዓለም ለማወቅ ሲሞክሩ ከእግዚአብሔር እውነት ጋር በጥብቅ መቆራኘታቸው ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ወጣቶች መካከል ያለው ጠንካራ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የወደፊቱን ትውልድ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ጥልቅ መሰረት እንዲኖራቸው  የሚያስችል ጠንካራ እድል ይፈጥራል።

  > ወጣት አማኞች መጽሐፍ ቅዱስን የህይወት መመሪያቸው  እንዲያደርጉ እና የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት ሕይወታቸውን እንዴት ሕይወታቸውን በሚቀይር መንገድ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ ማሳየት እንችላለን?

- **ወጣቶች እንዲናገሩ አሰልጥኗቸው**
  አብዛኞቹ ወጣቶች ከመልካም የቤተሰብ ግንኙነቶች ጎን ለጎን ጥብቅ ጓደኝነቶች እንዳላቸው ማየቱ አሳዛኝ ነው። ብዙውን ጊዜ፣ በማንነት እና በግንኙነት ጉዳዮች ላይ በአካልም ሆነ በኢንተርኔት ምክርን ከእነዚህ ጓደኞች ይፈልጋሉ። ለእነዚህ ውስብስብ ጉዳዮች መልስ ሲፈልጉ፣ የቤተሰብ አባላትን ወይም የሃይማኖት መሪዎችን በቀጥታ ማነጋገር ሁልጊዜ ምቾት ላይሰማቸው ይችላል። ይህም በእነዚህ ጠቃሚ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብን መምከር እንዲችሉ እኩዮቻቸውን ማብቃት አስፈላጊ መሆኑን ሊሰመርበት ይገባል።

  > በአዳጊ ወጣቶች የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያን ወጣቶች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ማንነት እንዲገነዘቡ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር የምንችለው እንዴት ነው? እና በአጠቃላይ  ወጣቶችን ከታመኑ አማካሪዎች እና ጓደኞች ጋር በእውነተኛነት መነጋገር እንዲችሉ ልናበረታታቸው እንችላለን?

- **የገጠር አካባቢዎች የበለጠ ይቸገራሉ**
  በገጠር ያሉ ወጣቶች ከከተማ እኩዮቻቸው ይልቅ በቤተሰብ እና በጓደኝነት ላይ አሉታዊ ልምዶቻቸውን ሪፖርት አድርገዋል። ለመንፈሳዊ እና ስሜታዊ ጤንነት ከሌሎች ጋር ህብረት ማድረግ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ከተረዳን፣ ይህ አሳሳቢ ነው። ወጣቶች ለሃይማኖታዊ እምነታቸው እና ልምምዳቸው ትልቅ ቦታ እንደሚሰጡ እናውቃለን። በገጠር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶች የሚገናኙበት እና ጠንካራ ግንኙነት የሚፈጥሩባቸውን ቦታዎች በመፍጠር ረገድ ሊያስቡበት ይገባል።

  > አብያተ ክርስቲያናት በማኅበረሰባቸው ውስጥ ጤናማ ቤተሰባዊ ተቋም እና ጠንካራ ጓደኝነት እንዲፈጠር እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ ይችላሉ?

# የግል ገጠመኞች እና ፈተናዎች

የኢትዮጵያ ሪፖርት

# እኛ ያገኘነው



**45%** የሚሆኑ ወጣቶች **ከብቸኝነት እና ከድብርት** ብዙዎች ደግሞ ከ**ከፍተኛ ጭንቀት ጋር እየታገሉ ነው።**

**ራስን የማጥፋት አደጋ አደንዛዥ እጽ ከመጠቀም፣ ስካር እና የወሲብ ጉዳዮችን ጨምሮ ከሌሎች** ፈተናዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው።

**21%** የሚሆኑ ወጣቶች **የራስን ሕይወትየማጥፋት ሐሳብ አድሮባቸዋል።**

**9% ራስን የማጥፋት ሙከራ** ማድረጋቸውን ዘግቧል።





**የተሰጡ ክርስቲያኖች** ልክ እንደሌሎች ወጣቶች **ለአእምሮ ጤና ትግሎች/ፈተናዎች የመጋለጥ እድል** ቢኖራቸውም **ወሲባዊ ድርጊቶችን የመፈፀም ዕድላቸው አነስተኛ ነው።**



**ወንዶች ከሴቶች የበለጠ** በቅርቡ **የወሲብ ፊልሞችን የመመልከት** ወይም **ወሲብ የመፈጸም እድላቸው ሰፊ ነው።**

**በገጠር** አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች **በሌሎች አካባቢዎች ካሉ ታዳጊዎች የበለጠ ከጋብቻ በፊት** ወሲብ ይፈጽማሉ።



# የአዕምሮ ጤና

ወጣቶች በህይወታቸው ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ስለግል ተሞክሯቸው እና ትግሎቻቸው እንዲነግሩን ጠይቀናቸው ነበር። ከወጣቶች መካከል ከግማሽ የሚበልጡት ብቸኝነትና ድብርት እንዳጋጠማቸው ገልጸዋል። በተጨማሪም ከ3 ወጣቶች ውስጥ 1 ከከፍተኛ ጭንቀት ጋር እየታገለ እንደሆነ ተናግረዋል።

## የአእምሮ ጤና ትግሎች

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-




ወጣቶች እያደጉ ሲሄዱ የአእምሮ ጤንነት ችግር በቋሚነት ይቀጥላል። ከተጠየቁት ውሰጥ ዕድሜያችው ከፍ ያለው ወጣቶች ብቸኝነት እንደሚሰማቸው ሪፖርት የማድረግ አጋጣሚያቸው ሰፊ ሲሆን ለጥያቄያችን መልስ የሰጡት ወጣቶች ደግሞ በትንሹም ቢሆን ከፍተኛ ጭንቀት እንደሚሰማቸው ሪፖርት አድርገዋል። በጥቅሉ ሲታይ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ብቸኝነት፣ ድብርት እና ከፍተኛ የሆነ ጭንቀት ያጋጥማቸዋል። በሃይማኖት ተቋማት መካከል የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ትግል ሲያሳልፉ፣ ወንጌላውያን በትንሹ ድብርት፤ ሙስሊሞች ደግሞ የብቸኝነትና የጭንቀት ስሜት ሪፖርት አድርገዋል። የሚያሳዝነው ግን የተሰጡ ክርስቲያኖች እንደሆኑ በሚናገሩ ወጣቶች መካከልም እንኳ እነዚህ ትግሎች ይታያሉ።

## የአእምሮ ጤና ትግል በእድሜ

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-



# የአእምሮ ጤና ተግዳሮቶች በጾታ

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-




# የአእምሮ ጤና ተግዳሮቶች በሐይማኖት

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-




# የአዕምሮ ጤና ተግዳሮቶች በመሰጠት

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-



# ራስን ማጥፋት

ወጣቶች ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ የራሳቸውን ሕይወት ስለማጥፋት አስበው ወይም የራሳቸውን ሕይወት ለማጥፋት ሙከራ አድርገው እንደሆነ ራሳቸው ሪፖርት እንዲያደርጉ ጠየቅናቸው። የሚያሳዝነው ግን ከ5 ወጣቶች መካከል ከ1 በላይ የሚሆኑት የራሳቸውን ሕይወት የማጥፋት ሐሳብ እንደነበራቸው ሪፖርት ሲያደርጉ ከ10 ወጣቶች መካከል 1 ደግሞ የራሳቸውን ሕይወት ለማጥፋት ሙከራ እንዳደረጉ ሪፖርት አድርገዋል።

## ራስን የማጥፋት አደጋ

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-

ራስን የማጥፋት ሃሳቦች ነበሩኝ




ራስን የማጥፋት ሙከራ አድርጌያለሁ




የራስን ሕይወት የማጥፋት አደጋ ወጣቶች ከሚጋፈጧቸው ሌሎች ትግሎች ጋር በጥብቅ የተገናኘ ነው። በቅርቡ ለመዝናኛነት በሚጠቀሟቸው ዕፆች የተጠቀሙ ጥናቱ ውስጥ የተሳተፉ ወጣቶች ራሳቸውን የመግደል ወይም ሙከራ የማድረግ አጋጣሚያቸው ሰፊ እንደሆነ ጥናታችን ያሳያል። አደገኛ ዕፅ ከሚወስዱ ወጣቶች መካከል 64% የሚሆኑት ራሳቸውን የማጥፋት ሐሳብ ያላቸው ሲሆን 55% የሚሆኑት ደግሞ ሙከራ አድርገዋል። ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች አደገኛ ሁኔታዎች ደግሞ ስካር፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የወሲብ ግንኙነት መፈጸም፣ ጸበኛ መሆን እና የወሲብ ፊልሞችን መመልከት ናቸው።

## 6 ራስን ከማጥፋት አደጋ ጋር የሚገናኙ ነገሮች



ወደ ሃይማኖታዊ ተቋማት ስንመጣ፣ ወንጌላውያን እና የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ራስን የማጥፋት አደጋ ሲዘግቡ ሙስሊሞች ደግሞ በጣም ዝቅተኛ መጠን እንዳላቸው ይናገራሉ። የተሰጡ ክርስቲያኖች ራስን የማጥፋት ሀሳቦች እና ሙከራዎች ከስም ክርስቲያኖች በመጠኑ ዝቅተኛ ደረጃን ያሳያሉ።

## ራስን የማጥፋት አደጋ በሃይማኖት

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-




## ራስን የማጥፋት አደጋ በመሰጠት

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ይህ አጋጥሞኛል፡-




ወጣቶች ራሳቸውን ለማጥፋት እንዲሞክሩ የሚያነሳሳቸው አንድ ክስተት ወይም አጋጣሚ አይደለም። ምንም እንኳን ልዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም እያንዳንዳቸው በሌላው ላይ ቀስ በቀስ የሚገነቡት ተከታታይ ትናንሽ ክስተቶች እና ሃሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ መረጃ እንደሚያሳየው አሳሳቢ ቁጥር ያላቸው በርካታ ወጣቶችን ተስፋ አስቆራጭ እርምጃ እንዲወስዱ የሚገፋቸው ከባድ ጨለማ ውስጥ መሆናቸውን ነው።

ሕይወታቸውን ለማጥፋት እስኪፈልጉ ድረስ በጣም ለተጎዱ ወጣቶች ከልባችን ልናዝን ይገባል። ራስን ስለ ማጥፋት ስናነሳ፣ በወረቀት ላይ የተጻፉ ቁጥሮችን አይደለም የምንመለከተው፤ ነገር ግን የእውነተኛ ሰዎችን ሕይወት ነው። ማንኛውም ቁጥር በጣም ብዙ እና ማንኛውም መቶኛ(%) በጣም ከፍተኛ ነው።

# የወሲብ ስሜት

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙት ዓመታት የሙከራ ጊዜያት ሲሆኑ ይህም የራስን የወሲብ ፍላጎት የመረዳት ልምምድንም ይጨምራል። ይህ በተለየ ሁኔታ ወጣቶች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉን የጠየቅንበት ጉዳይ ነበር። ጥናቱ ውስጥ የተሳተፉት አብዛኞቹ ወጣቶች ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም ምንም ችግር የለውም ብለው ያስባሉ።

## ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም

ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ምንም ችግር የለውም ብለው ያምናሉ?




የራሳቸው ወሲባዊ ልምምድ በተመለከተ በጥናቱ ከተሳተፉት ወጣቶች መካከል 15% የሚሆኑት ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ የወሲብ ግንኙነት እንዳደረጉ ይናገራሉ። ወሲብ ልምምድ ውስጥ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ የራሳቸውን ትርጓሜ ሰጥተዋል። ይህ አሃዛዊ መረጃ ከጋብቻ በፊት የሚደረግን ወሲባዊ ግንኙነትን ብቻ የሚመለከት መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ያገቡ ወጣቶች ከእነዚህ ጥያቄዎች እንዲገለሉ ተደርገዋል።

ወንዶች በቅርብ ጊዜ የወሲብ ግንኙነት የማድረግ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። በአጠቃላይ የወሲብ ልምምድ እድሜ ሲጨምር ይጨምራል። የወሲብ ልምምድን በተመለከተ በገጠር አካባቢ ከተመዘገበው ይልቅ በከተማ ደረጃ የተመዘገበው ዝቅተኛ ነው። የኦርቶዶክስ ክርስትና የወሲብ ልምምድ ውስጥ በመግባት ከፍተኛ የሆነው የሃይማኖት ተቋም ነው። የተሰጡ ክርስቲያኖች ዝቅተኛ የወሲብ ልምምድ እንዳላቸው ተናግረዋል።

## ወሲብ ፈጽሜያለሁ

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ፡-



## የወሲብ ልምምድ በዕድሜ

7%
ሴቶች

18%
ወንዶች

## የወሲብ ልምምድ በዕድሜ

13-16 5%
17-20 11%
21-25 26%

## የወሲብ ልምምድ በአካባቢ

19%
ገጠር

13%
ከተማ ቀመስ

8%
ከተማ

## የወሲብ ልምምድ በኃይማኖት

ወንጌላውያን 8%
ኦርቶዶክስ 19%
ሙስሊም 14%

በቅርብ ጊዜ ውስጥ የወሲብ ግንኙነት አድርጌአለሁ፡-

የተሰጡ ክርስቲያኖች 6%

የስም ክርስቲያኖች 18%

ከ3 ክርስቲያን ወጣቶች 1 የወሲብ ፊልሞችን እንደሚመለከቱ ተናግረዋል። ሐቀኝነታቸውን ብናደንቅም፣ ይህ ባህሪ ግን የሚያሳስብ ነው። በሚያዛዝን ሁኔታም ክርስቲያኖች፣ የተሰጡ ክርስቲያኖችን ጨምሮ፣ ከሙስሊም ጓደኞቻቸው ይልቅ የወሲብ ፊልሞችን በብዛት ይመለከታሉ።

## የወሲብ ፊልም አጠቃቀም በሐይማኖት

| | |
|---|---|
| ወንጌላውያን | 32% |
| ኦርቶዶክስ | 34% |
| ሙስሊም | 18% |

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ የወሲብ ፊልሞችን ተመልክተዋል?

| | |
|---|---|
| የተሰጡ ክርስቲያኖች | 32% |
| የስም ክርስቲያን | 34% |

# ሌሎች ተግዳሮቶች

ወጣቶች የሚያጋጥሟቸው ፈተናዎች ሁልጊዜ ከውጪ የሚታዩ አይደሉም። ነገር ግን ውጫዊ መገለጫዎች ሊኖሯቸው ይችላሉ። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች አደንዛዥ እፅን መጠቀም (6%) እና ስካር/የመጠጥ ሱስ (9%) ተጠቂ እንደሆኑ ተናግረዋል። የአልኮል አጠቃቀም እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ይጨምራል፣ አደንዛዥ ዕፅን መጠቀም ግን ይቀንሳል። ከሃይማኖት ተቋማት መካከል የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች የመጠጥ እና የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኛ የመሆን ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ሙስሊሞችም ደግሞ በትንሹ። የተሰጡ ክርስቲያኖች ከእነዚህ ከሁለቱም ልምምዶች ውስጥ የመሳተፍ እድላቸው ከስም ክርስቲያኖች ያነሰ ነው።

## የአልኮል መጠጥና የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ:-

| | 13-16 | 17-20 | 21-25 |
|---|---|---|---|
| ሰክረው ነበር | 5% | 8% | 16% |
| ለመዝናኛ ዓላማዎች የሚያገለግሉ አደንዛዥ እጾች | 9% | 5% | 4% |

## አልኮል እና አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ፡-




## አልኮል እና አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ፡-




# ጥቃት

የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ ወጣቶች በማኅበረሰባቸው ወይም በኢንተርኔት አማካኝነት ከሰዎች ጋር መጥፎ ሁነቶች አጋጥሟቸዋል። ከወጣቶች መካከል 15 በመቶ የሚሆኑት በቅርቡ በ ሰው ጥቃት እንደደረሰባቸው ሪፖርት አድርገዋል። የጥቃቱ ቁጥር እድገት ከፆታና ከዕድሜ ጋር የሚጣጣም ነው።

## ጥቃት በጾታ

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ በኢንተርኔት መስመር ወይም በአካል በሆነ ሰው ጥቃት አድርሶቦታል?




**15%** የሚሆኑት ወጣቶች ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ጥቃት የነበረው አጋጥሟቸዋል።

## ጥቃት በእድሜ

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ በኢንተርኔት መስመር ወይም በአካል በሆነ ሰው ጥቃት አድርሶቦታል?



# ማጠቃለያ

ይህ መረጃ በወጣቶች ዓይን ሲታይ ሕይወት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ አሳዛኝ መግለጫ ሊሆን ይችላል። የወጣቶች የዕለት ተዕለት ተሞክሮዎች እና ትግሎች ከአቅም በላይ ሊመስሉ ይችላሉ፣ ነገር ግን ወደ ተግባር ከመዞራችን በፊት በማዳመጥ እና በመረዳት መጀመር አስፈላጊ ነው። ልናስብባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ከዚህ በታች ቀርበዋል፦

- **ድጋፍ ለሴቶች እና ለወንዶች የሚያስፈልገው በተለያየ መንገድ ነው**
  የግል ትግል እንደ የጾታው ልዩነት እንዳለው የማይካድ ነው። እንስቶቹ ይበልጥ ከብቸኝነት፣ ከመንፈስ ጭንቀትና ድብርት ጋር እየታገሉ ሲሆን፤ ወንዶች ደግሞ በጾታዊ ስሜትና ወሲባዊ ሥዕሎች በመመልከት ሱስ የተነሳ ብዙ ትግል ውስጥ ወደ መግባት ያጋድላሉ። ወጣቶችን ለየት ባለ ሁኔታ  ደቀ መዝሙር ለማድረግ የሚያስፈልጉትን መንገዶች እና ከዚህ ትውልድ ጋር አብረው መራመድ የሚችሉ አማካሪዎችን እንዴት ማሳደግ እንደምንችል አስቡ።

  ወጣቶች የሚያጋጥሟቸውን ፈታኝ ሁኔታዎች ለመቋቋም አብያተ ክርስቲያናት ከጎናቸው መሆናቸውን የምትመለከቱት እንዴት ነው?

- **ራስን የማጥፋት አደጋ ከባድ ነው**
  አንዳንድ ወጣቶች በጣም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ውስጥ ከመሆናቸውም በላይ ሕይወታቸውን ስለማጥፋት እያሰቡ ነው። ይህ ትግል በኢትዮጵያ በሁሉም የእድሜ ክልሎች፣ በሁለቱም ፆታዎች እና የሀይማኖት ተቋማት ውስጥ ይገኛል። ወጣቶችን ደቀ መዝሙር በምናደርግበት ወቅት የሚያሳስቧቸውን ነገሮች በቁም ነገር ልንመለከት እና በጌታ ኢየሱስ ተስፋ ልናበረታታቸው ይገባል።

  ታዲያ እነዚህን አሳሳቢ ሁኔታዎች በንቃት መከታተልና የምንቀርባቸውን  ወጣቶች ሁለንተናዊ  እንክብካቤ እንዲያኙ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?

- **ከእይታ የተደበቁ የወሲብ ምስሎች አሉ**
  ይህ በዓለም ዙሪያ እንዲሁም በአፍሪካ ለሚገኙ አዳጊ ወጣቶች ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ሃይማኖተኝነት ወጣቶችን ከወሲብ ፈተና አይጠብቃቸውም። ይህም ጽኑ ፍላጎት በፈጣኑ ኢንተርኔት አቅራቢነት የወሲብ ምስሎቹን ስለሚያገኙ ይሳካል። ይህ ፈጣን አቅርቦት የሥነ ምግባር እሴቶቻቸውን ሊያዳክምባቸውና ከእምነታቸው ጋር ወደ ሚጋጩ ምርጫዎች ይመሯቸዋል እናም ብዙውን ጊዜ የጥፋተኝነት፣ የኀፍረትና ግራ መጋባት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል።

  ወጣቶች እግዚአብሔርን በመፍራት እና ራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን በሚያስከብሩ መንገዶች እንዲኖሩ መርዳት የምንችለው እንዴት ነው?

- **የተሰጡ ክርስቲያኖችም ይህ ተግዳሮት ይገጥማቸዋል**
  በዛሬው ጊዜ ያሉ ወጣቶች ብቸኝነት፣ ጭንቀት፣ ወሲባዊ ምሥሎችንና ፊልሞችን መመልከት በተጨማሪም የራሳቸውን ሕይወት ለማጥፋት እስከማሰብ ድረስ የተለያዩ ፈታኝ ሁኔታዎች እንደሚያጋጥሟችው የታወቀ ነው። የተሰጡ አማኞች መሆን የግድ ከእነዚህ ችግሮች ሊከላከልላቸው አይችልም። ይህ መረጃ ወጣቶች የወንጌልን ተስፋ ዕለት ከዕለት ከሚያጋጥሟቸው እውነተኛ ጉዳዮች ጋር እንዲያያይዙ መርዳት አስፈላጊ መሆኑን ያሳየናል። ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ወጣቶች በነዚህ ፈታኝ ሁኔታዎች እንዲወጡ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመርዳት ወጣቶች ተሞክሯቸውንና ትግሎቻቸውን በግልጽ ለክርስቲያን እኩዮቻቸውና ለመሪዎች መናገር የሚያስችላቸው ነጻነት እንዲኖራቸው ማድረግ አለባት።

  ወጣቶች የሚያጋጥሟቸውን ፈታኝ ሁኔታዎች ከመደበቅ ይልቅ እርዳታ እንዲፈልጉ እና በአስተሳሰባቸውና በድርጊታቸው ከማፈር ይልቅ የሚደግፉቸው እንዳለ እንዲሰማቸው ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?

# የዲጂታል ግንኙነት እና ተጽዕኖ

የኢትዮጵያ ሪፖርት

# እኛ ያገኘነው



**82%** የሚሆነው ወጣት የራሱ **ስልክ አለው** እድሜያችው እየጨመረ ሲሄድ ይጨምራል።



**በከተማ** አካባቢዎች የሚገኙ ወጣቶች **ስማርት ስልክ የመያዝ ዕድላቸው ሰፊ ነው።**

በጥናቱ ከተካፈሉት መካከል **በአማካይ 3 ሰዓት ከ39 ደቂቃ** ኢንተርኔት **ላይ እንድሚያሳልፉ** ሪፖርት ተደርጓል።



**ዕድሜያቸው የጨመረ** ወጣቶች **ማህበራዊ ሚዲያን የበለጠ እንድሚጠቀሙ** እና በ ሕ ይወታቸውም ላይ በጎ ተጽእኖ **እንዳለው ይናገራሉ።**





ወጣቶች **ማህበራዊ ሚዲያ እንደሚያግዛቸውም እንደሚጎዳቸውም** አምነው ይቀበላሉ።



ወጣቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በኢንተርኔት **ማህበራዊ ሚዲያ** ወይም **መልዕክት በማውራት** ነው።



# ወጣቶች እና ቴክኖሎጂ

ኢንተርኔት ይህንን ትውልድ በእርግጥ እየቀረጸው ያለ ነገር ነው። ወጣቶች በጣታቸው ጫፍ ላይ መረጃ፣ አስተያየትና ምሪቶችን ማግኘት ይችላሉ። ይህ ግን በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እያሳደረ ነው?

ምን ያህል ወጣቶች ስልክ እንዳላቸው፣ ኢንተርኔት ላይ ምን ያህል ጊዜ እንደሚያሳልፉ፣ እና ማኅበራዊ ድረ ገጾችን እንዴት እንደሚጠቀሙ ለማወቅ ፈልገን ነበር፤ በጥናቱ የተሳተፉ አብዛኞቹ ወጣቶች (82%) ስልክ እንዳላቸው ተናግረዋል። ይህም እድሜያቸው እየጨመረ ሲሄድ የሚጨምር ነው። ምንም እንኳን ይህ በገጠራማ አካባቢዎች በሚኖሩ ወጣቶች ያልተለመደ ቢሆንም።[1] ተንቀሳቃሽ ስልክ ያላቸው አብዛኞቹ ሰዎች ስማርት ስልክ አላቸው።







## ስልክ አለኝ




1 ይህ አኃዛዊ መረጃ ሀገራዊ ቡድኑ ከጠበቀው በላይ ነበር፤ ምናልባትም ጥያቄ ከቀረበላቸው ሰዎች መካከል አብዛኞቹ ሰዎች ከተማ ቀመስ በሆኑ እና በከተሞች ውስጥ የሚገኙት ስለሆኑ ይሆናል።

## ስማርት ስልክ አለኝ




አብዛኛውን ጊዜ ወጣቶች ኢንተርኔት የሚጠቀሙት ቤታቸው ሆነው ነው፤ ይሁን እንጂ አንዳንዶች ኢንተርኔት የሚጠቀሙት በሞባይል ስልካቸው አማካኝነት ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። በርካታ ወጣቶች ኢንተርኔት ለማግኘት ኢንተርኔት ካፌ፣ ትምህርት ቤት ወይም ቤተ ክርስቲያን መሄድ አለባቸው።

## ኢንተርኔት የማግኘት እድል

ኢንተርኔት የምታገኘው የት ነው? (የሚመለከተውን ሁሉ ይምረጡ)[1]




ወንዶች በኢንተርኔት ካፌዎች ወይም በሌሎች ሕዝብ በሚጠቀምባቸው አካባቢዎች ኢንተርኔት የመጠቀም አጋጣሚያቸው ከሴቶች ይበልጣል። በገጠራማ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ኢንተርኔት እንደማያገኙ የመናገር አጋጣሚያቸውም ሰፊ ነው።

1 ወጣቶች ለዚህ ጥያቄ ከአንድ በላይ መልስ ሊመርጡ እንደሚችሉ አስተውሉ፤ ይህም የውጤቱ አጠቃላይ ድምር ከ 100% በላይ እንዲሆን ያደርጋል።

## ኢንተርኔት የማግኘት እድል በጾታ

ኢንተርኔት የምታገኙት የት ነው?[1]




## ኢንተርኔት የማግኘት እድል በቦታ

ኢንተርኔት የምታገኙት የት ነው?




1 ብዙ ጊዜ የተመረጡት ሦስቱ ዋና መልሶች እነዚህ ናቸው።

# ወጣቶች እና ኢንተርኔት

ወጣቶች በኢንተርኔት ላይ ምን ያህል ጊዜ እንደሚያሳልፉና ምን በማድረግ እንደሚያሳልፉ ለማወቅ ጓጉተን ነበር። በኢትዮጵያ በጥናቱ የተሳተፉ ወጣቶች ማህበራዊ ድረ-ገፆችን በመጠቀም፣ በጽሁፍ በማውራት፣ ቪድዮዎችን በማየት እና ጨዋታ በመጫወት በየቀኑ በርካታ ሰዓታት በኢንተርኔት እንደሚያሳልፉ ሪፖርቱ ያሳያል። ኢንተርኔት ላይ ጊዜን ማሳለፍ በዕድሜ፣ በፆታና በሃይማኖት ተቋማት መካከል ተመሳሳይ ነው። የሚገርመው ነገር በገጠራማ አካባቢዎች የሚኖሩ ወጣቶች ከተማ ቀመስ በሆኑ እና ከከተሞች ይልቅ በኢንተርኔት ላይ አጠቃላይ ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉ ሪፖርት አድርገዋል።

## የኢንተርኔት ላይ ቆይታ[1]

በቀን ውስጥ በኢንተርኔት ላይ ምን ያህል ሰዓት ያሳልፋሉ? (ሁሉንም እንቅስቃሴዎች ያካትታል)




## የኢንተርኔት መስመር ላይ እንቅስቃሴዎች

በመደበኛ ቀን ምን ያህል ጊዜ ያሳልፋሉ...




1 በኢንተርኔት ስለምናሳልፈው ጊዜ የሚነሳው ይህ ጥያቄ በትምህርት ቤት ኢንተርኔት በመጠቀም የሚያሳልፈውን ጊዜ ይጨምራል።

ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ብዙ ጊዜ በጽሁፍ መልዕክት የሚያወሩ ሲሆን የከተማ ወጣቶች ደግሞ በሌሎች አካባቢዎች ከሚገኙ ወጣቶች ይልቅ በጽሁፍ መልዕክት ያወራሉ። የከተማ ወጣቶች ጌም በመጫወት የሚያሳልፉት ጊዜ በጣም ሰፊ ነው። ምድቦቹን በዕድሜ መከፋፈል እምብዛም ልዩነት የሌላቸው ቢሆኑም በጥቅሉ ግን ውጤቱ ከታች ተካትቷል።

## በማህበራዊ ድረ ገጽ

በመደበኛ ቀን፣ በግምት ለምን ያህል ሰዓት ማህበራዊ ድረ ገጽ ትጠቀማለህ?




## በጽሁፍ መልዕክት በማውራት

በመደበኛ ቀን፣ በኢንተርኔት መስመር ላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመነጋገር፣ መልእክት በመላላክ ወይም በቪዲዮ በመወያየት ምን ያህል ጊዜ ያጠፋሉ?



## ቪዲዮችን ለመመልከት

በመደበኛ ቀን፣ በኢንተርኔት የሚተላለፉ ቪዲዮዎችን ወይም ፊልሞችን (ዩቲዩብ፣ ኔትፍሊክስ፣ ወዘተ) በመመልከት በግምት ምን ያህል ያሳልፋሉ?




## ጌም መጫወት

በመደበኛ ቀን፣ ጌሞችን በመጫወት (ፕሌይስቴሽን፣ ኤክስ ቦክስ፣ ኮምፒውተር፣ ስማርትፎን ወዘተ) በግምት ምን ያህል ሰዓት ያሳልፋሉ?



# ወጣቶች እና ማህበራዊ ድረ ገጽ

ወጣቶች ማህበራዊ ድረ ገጽ በሕይወታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ በተመለከተ የተደበላለቀ ስሜት አላቸው። ከ5 ሰዎች አንዱ በጭራሽ አይጠቀምም። እንደሚጠቀሙ ከሚናገሩ ሰዎች መካከል አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት ብቻ እርካታ እንደሚሰጣቸው ይናገራሉ፤ አብዛኞቹ ሰዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ መጥፎ ስሜት እንደሚሰማቸው ይናገራሉ። ወንዶችና ሴቶች በማኅበራዊ ድረ ገጾች ላይ ተመሳሳይ ተሞክሮዎችን ሪፖርት ሲያደርጉ በገጠር የሚኖሩ ሰዎች ግን ከአሉታዊ ውጤቶች ጋር የማያያዝ አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው።

## የማህበራዊ ድረ ገጽ እርካታ

ማህበራዊ ድረ ገጽ  በህይወቴ እርካታ እንዲሰማኝ ረድቶኛል።




## በማህበራዊ ድረ ገጽ እርካታ ማጣት

ማህበራዊ ድረ ገጽ ሀዘን፣ ጭንቀት ወይም ድብርት እንዲሰማኝ አድርጎኛል።




## የማህበራዊ ድረ ገጽ ተፅእኖዎች በአካባቢ

ማህበራዊ ድረ ገጽ አንዳንድ ጊዜ ወይም ብዙ ጊዜ ያሳዝነኛል፣ ያስጨንቀኛል፣ ወይም ድብርት እንዲሰማኝ ያደርገኛል።



## እኔ በዋነኝነት ማህበራዊ ድረ ገጽን የምጠቀመው[1]

| | |
|---|---|
| መረጃ እንዳገኝ ይረዳኛል | 47% |
| ከጓደኞቼ እና ከቤተሰብ ጋር እንድገናኝ | 32% |
| አስቂኝ ወይም አዝናኝ ነገሮችን ለማግኘት | 26% |
| ታዋቂ ሰዎችን እና የሚመቹኝን ምርቶች ለመከተል | 7% |
| ስለ እኔ ለዓለም የበለጠ ለማሳወቅ | 3% |
| ማህበራዊ ድረ ገጽ አልጠቀምም | 17% |

አብዛኞቹ ወጣቶች በማኅበራዊ ድረ ገጾችን የሚጠቀሙት ዓለም ዓቀፍ መረጃዎች እንዲደርሷቸው ወይም ከጓደኞቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለመገናኘት መሆኑን ሪፖርት አድርገዋል። ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ከሚወዷቸው ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመቀጠል የመጠቀም እድላቸው ሰፊ ነው። ከ13 እስከ 16 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ልጆች መካከል የማኅበራዊ ድረ ገጽ አጠቃቀም በጣም ዝቅተኛ ነው። ዕድሜያቸው ከፍ ያለው በጥናቱ የተሳተፉ ወጣቶች ዓለም ዓቀፍ መረጃዎች እንዲደርሷቸው እና ከጓደኞቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለመገናኘት ወደ ማህበራዊ ድረ ገጾች እንደሚያዞሩ ተናግረዋል። አነስ ያሉት ወጣት ተጠቃሚዎች አስቂኝ ወይም አዝናኝ ነገሮችን የመመልከት እድላቸው ሰፋ ያለ ነው።

## የማህበራዊ ድረ ገጽ አጠቃቀም በፆታ

ማህበራዊ ድረ ገጽን በዋናነት የምጠቀመው ለ...[2]

| | ሴቶች | ወንዶች |
|---|---|---|
| ዓለም ዓቀፍ መረጃዎችን ለማግኘት ይረዳኛል | 46% | 48% |
| ከጓደኞቼ እና ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት | 37% | 26% |
| አስቂኝ ወይም አዝናኝ ነገሮችን ለማግኘት | 26% | 27% |
| ማህበራዊ ድረ ገጽ አልጠቀምም | 18% | 16% |

1 ወጣቶች ለዚህ ጥያቄ እስከ ሁለት መልሶች መምረጥ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ ስለዚህ አጠቃላይ ድምር ከ 100% በላይ ይጨምራል።
2 ብዙ ጊዜ ከተመረጡት አራቱ ምርጥ መልሶች ተዘርዝረዋል።

# የማህበራዊ ድረ ገጽ አጠቃቀም በዕድሜ

ማህበራዊ ድረ ገጽን በዋናነት የምጠቀመው ለ...[1]




1 ብዙ ጊዜ ከተመረጡት አራቱ ምርጥ መልሶች ተዘርዝረዋል።



# ማጠቃለያ

ከዲጂታል መድረኮች ጋር የሚኖር የማያቋርጥ ግንኙነት ለዛሬዎቹ ወጣቶች የሕይወት መንገድ እየሆነ መጥቷል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ስልክ ባለቤት የሆኑ እና የኢንተርኔት አገልግሎት እያገኙ ያሉ የኢትዮጵያ ወጣቶች ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል። ይህን አዲስ እውነታ ተቀብለው በእነዚህ ዲጂታል መድረኮች ላይ ከወንጌል መልእክት ጋር በሚጣጣም መንገድ እንዲሳተፉ እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?

- **ዲጂታል እድሎችን ይጠቀሙ**
  ቴክኖሎጂ ወደዚህ ትውልድ ለመድረስ የሚያስችል ጠንካራ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። ብዙ ወጣቶች በተለይም በከተሞች አካባቢ ኢንተርኔት በመጠቀም የሚያገኟቸውን መተግበሪያዎች፣ ድረ ገፆች እና ማህበራዊ ሚዲያ የመሳሰሉትን መድረኮች በመጠቀም የሚያሰገኟቸ ውን ጥቅሞች በማግኘት ላይ ይገኛሉ። በተለይ በዚህ ጥናት የተሳተፉ ወጣቶች ማኅበራዊ ድረ ገጾችን የሚጠቀሙት ዓለም አቀፍ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት እንደሆነ ነግረውናል። በኢንተርኔት ላየ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ሕይወታቸውን ለመምራት እና ይህን ዓለም ለመረዳት መረጃ በመፈለግ ነው።

  > የወንጌል ይዘት ያላቸው ነገሮች እና እነሱ አባል ሊሆኑ የሚችሉባቸው ሕይወት ሰጪ የኢንተርኔት ማህበረሰቦች ማግኘት እንደሚችሉ እንዴት ልናረጋግጥ እንችላለን?

- **ውጥረቱን ተከተሉ**
  ይህ ትውልድ ዲጂታልን እየተቀበለ ቢመስልም አንዳንድ ወጣቶች እነዚህ መገልገያዎች ወደ ሕይወታቸው እያመጡ ያሉትን ውጥረት ይገነዘባሉ። አንዳንዶች ማኅበራዊ ድረ ገጾች በሕይወታቸው እርካታ እንዲሰማቸው እንደሚያደርጋቸው ቢናገሩም ሌሎች ግን ከአሉታዊ ስሜቶች ጋር ያያይዙታል። የዲጂታል አማራጮች ስጦታዎች እና ፈተናዎች ዛሬም ሆነ ወደፊት ለወጣቶች የሚቀሩ አይደሉም።

  > በዲጂታል ዓለም ውስጥ ጠልቆ መግባትን በማስተዋል ወጣቶች የዲጂታሉን ዓለም በጤናማ መንገድ እንዲጠቀሙብት እንዴት መርዳት እንችላለን?

- **ለወደፊቱ ጊዜ የሚሆን አቋም**
  የዲጂታሉ ዓለም ሁላችንም ወደፊት የምንቀላቀልበት ሁነት ነው፣ ወጣቶች በዚህ መንገድ ቀድመውን መጓዝ ጀምረዋል። ይህን ማስቆም አንችልም፣ ነገር ግን ትውልዱን እኛ አካል ላልሆንንበት እና ለማንረዳው የዲጂታል ዓለም ከማጣት ይልቅ፤ እነርሱ ጋር ይህን ጉዞ መቀላቀልን መምረጥ እንችላለን። እንደ ቤተሰቦች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ እና የአገልግሎት ሰራተኞች፣ አለም እንዴት እየተለወጠ እንዳለ እና እኛ እንዴት መለወጥ እንዳለብን ማሰብ ያስፈልገናል።

  > ከዚህ ትውልድ ጋር የዲጂታል ዓለሙን እንዴት መቀላቀል እና ጥበብንም ሆነ አዳዲስ ነገሮችን ወደዚህ መድረክ ማምጣት እንችላለን?

# የወደፊቱን ጊዜ መመልከት

የኢትዮጵያ ሪፖርት

# እኛ ያገኘነው

በአጠቃላይ ወጣቶች የወደፊት ህይወታቸውን እና **የሥራ ዕድላችውን** ሲያስቡ **የተጋነነ እና ብሩህ የሆነ ተስፋ** አላቸው።

በብዛት የወደፊት ሙያቸውን ሲያሰቡ **ብሩህ ተስፋ የሚታያቸው ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ናችው።**



በጥናቱ የተሳተፉ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በጣም የሚጨነቁት **የወደፊት ሙያቸው ለሌሎች ሰዎች የሚጠቅም መሆን አለመሆኑ ላይ ነው።**

በተጨማሪም በስራዎቻቸው**መደሰትን** ይፈልጋሉ።



ወጣቶች በጣም የሚፈልጓቸው ሙያዎች **የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት** ወይንም **ህክምና** ናችው።

# የወደፊት የስራ ሁኔታ አመለካከት

በጥናቱ የተሳተፉ ወጣቶች በሙሉ ማለት ይቻላል (97%) ወደፊት ክፍት የሥራ ዕድል እንደሚጠብቃቸው ያምናሉ። በሁሉም የሃይማኖት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች በተመሳሳይ ሁኔ ታ አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጡት ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም ሙስሊሞች ግን መለስተኛ አመለካከት አላቸው።

## ወደፊት የሥራ ዕድል እንደማገኝ አምናለሁ







ምንም እንኳን ወጣቶች ከፊታቸው ምን እንደሚጠብቃቸው ባያውቁም የወደፊት ሙያቸው ምን እንዲሆን እንደሚፈልጉ ያውቃሉ። ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚስጡት ነገር ሌሎችን መርዳት ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የሚሰጡት ደግሞ የሚያስደስታቸውን ሥራ መስራት ነው። ሥራው የሚከፍለው ደመወዝ እና ለሙያው የሚሰጠው ክብርም በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን ዋጋ የሚሰጡት ነገር ነው።

እነዚህ ወጣቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች በዕድሜ፣ በፆታ ወይም በአካባቢ ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ የገጠር አካባቢ ወጣቶች ግን ከሌሎች አካባቢ ወጣቶች የበለጠ የሚያሳስባቸው ሥራ ማግኘት ነው።

## ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የስራ ዘርፍ ምርጫዎች




## ቅድሚያ የሚሰጣቸው የስራ ዘርፍ ምርጫዎች በአካባቢ




## ስድስት ከፍተኛ የተመረጡ ሙያዎች

ለወደፊት ራሳችሁን ልታሳድጉበት የምትፈልጉት ሙያ የትኛው ነው?[1]

**22%** የቤተክርስቲያን አገልግሎት

**16%** ዶክተር

**14%** ስራ ፈጣሪ

**9%** ፕሮፌሽናል ስፖርቶች

**8%** ምህንድስና

**8%** ስነ-ጥበብ እና ሙዚቃ

1 ስድስቱን ከፍተኛ የተመረጡ ሙያዎች ከ 20 የሙያ ምርጫዎች ዝርዝር ውስጥ ለማውጣት ይቻላል። ወጣቶች እስከ ሁለት የመልስ አማራጮችን መምረጥ ይችላሉ።

# ከፍተኛ የስራ ዘርፍ ምርጫዎች በጾታ

| ልጃገረዶች | ወንዶች |
|---|---|
| 1 የቤተክርስቲያን አገልግሎት | 1 የቤተክርስቲያን አገልግሎት |
| 2 ዶክተር | 2 መሐንዲስ |
| 3 የስራ ፈጣሪ | 3 ፕሮፌሽናል ስፖርቶች |
| 4 ስነ ልቦና | 4 ኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ/ ሶፍትዌር ማበልጸግ |

በአለም አቀፍ የGYC ጥናታችን በአፍሪካ የሚገኙ ወጣቶች ከአለም አቀፍ እኩዮቻቸው የበለጠ ስራ ለመፍጠር ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው።[1] ይህ በኢትዮጵያም ቢሆን እውነት ነው። በጥናቱ ውስጥ ከተሳተፉት ወጣቶች መካከል አብዛኞቹ (86%) ወደፊት አንድ ንግድ ለመጀመር ወይም የራሳቸውን ድርጅት ለመክፈት ይፈልጋሉ። ሴቶችና ወንዶችም ተመሳሳይ የሆነ የራሳቸውን ስራ የመፍጠር ፍላጎት አላቸው። ዕድሜ እየጨመረ ሲሄድ የራሳቸውን ስራ የመፍጠር ፍላጎታቸውም ይጨምራል።

**28%** የሚሆኑት ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ መሰማራት ይፈልጋሉ።

# የስራ ፈጠራ

ወደፊት ንግድ መጀመር ወይም የራሴን ድርጅት ባለቤት መሆን እፈልጋለሁ።

| 84% | 86% | 89% |
|---|---|---|
| 13-16 | 17-20 | 21-25 |

**86%** የሚሆኑት በጥናቱ የተሳትፉ ወጣቶች ስራ ፈጣሪ የመሆን ዓላማ አላቸው።

1 OneHope. (January 2021). Global Youth Culture, Africa Report. www.globalyouthculture.net, 66.

# ማጠቃለያ

በጥናቱ ተሳትፈው የተመለከትናቸው ወጣቶች ለወደፊት ሕይወታቸው ብሩህ አመለካከትና ምኞት ያላቸው ሲሆን፤ ለዓላማ መር ሕይወት ቅድሚያ የሚሰጡ እና እርካታን የሚጨምርላቸው የራሳቸውን ስራ ለመፍጠር የሚፈልጉ ናቸው። በአካባቢያቸው፣ በፆታቸውና በሃይማኖታቸው የተለያዩ ቢሆኑም ለራሳቸውም ሆነ ለአገራቸው ትርጉም ያለው የወደፊት ሕይወት ለመቅረጽ ያላቸውን ቁርጠኝነት በጉልህ የሚታይ ነው።

- **ጥሩ አመለካከትን ማዳበር**
  ወጣቶች ስለ ወደፊቱ ጊዜ ብሩህ አመለካከት ያላቸው ሲሆን 97 በመቶ የሚሆኑት የሥራ ዕድል እንደሚያገኙ እርግጠኞች ናቸው። አብያተ ክርስቲያናት፣ ሚኒስትሪዎች፣ እና የማህበረሰብ መሪዎች ወንጌል በሁሉም የሕይወት ደረጃ ላይ ዘላቂ አላማ እና ደህንነት እንዴት እንደሚሰጥ በማሳየት ይህንን ብሩህ አመለካከት ለማበረታታት እድል አላቸው። የእኛ ድርሻ ወጣቶችን ከእሴቶቻቸው ጋር የሚጣጣሙ እና በወንጌል ውስጥ የሚገኘውን ተስፋ እና አላማ የሚያንጸባርቁ ሙያዎችን ለመከተል የሚያስችላቸው አቋም እንዲኖራቸው ማብቃት ነው።

  > ወጣቶች ተስፋ የሚያደርጉትን ስራ እግዚአብሔር ለእነርሱ ካለው ታላቅ እቅድ ጋር እንዲያያይዙ ልንረዳቸው የምንችለው እንዴት ነው?

- **ስራችንን ከዋና ዋና እሴቶች ጋር ማስማማት**
  ወጣቶች ወደፊት ስለሚሰማሩበት የሥራ መስክ ሲያስቡ ቅድሚያ ሊሰጡ የሚገባው ነገር ሌሎችን መርዳትና በሥራቸው መደሰት እንደሆነ ከጥናቱ መረዳት ችለናል። አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮሩ የሥራ መስኮች እንደሆነ ከጥናቱ መረዳት ችለናል በተጨማሪም በገጠር አካባቢ የሚያጋጥሙ ፈታኝ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፤ ለምሳሌ የስራ እድል ውስንነት፤ ትርጉም ያለው የስራ መስክ በመፍጠር ምቹ ከባቢን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ከወጣቶች ጋር አብሮ በመስራት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣ በጤና፣ በንግድ ወይም በማንኛውም መስክ ተሰማርተው የሚያከናውኑት ሥራ ሌሎችን ለማገልገልና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ለመመሥከር የሚያስችል ጠንካራ መንገድ መሆኑን እንዲገነዘቡ ልንረዳቸው እንችላለን።

  > ወጣቶችን በማንኛውም ሥራ ተሰማርተው ሌሎችን በማገልገል የክርስቶስን ፍቅር እንዲያንጸባርቁ እና ጥሪውን እንዲፈጽሙ እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

- **የሥራ ፈጣሪዎችን ዓላማ መደገፍ**
  86% ወጣቶች ንግድ ለመጀመር በሚመኙበት ሁኔታ፣ የግል ስራ ፈጠራ የግል እድገትን እና የወንጌል ተፅዕኖን ጎን ለጎን ለማራመድ ጠንካራ እድልን ይፈጥራል። ሚኒስትሪዎች እና ድርጅቶች ስራ ፈጣሪ ወጣቶች እምነትን እና የግል ንግድን እንዴት በአንድ ላይ ለማስኬድ እንደሚችሉ ለማገዝ ስልጠና፣ መርጃ መሳሪያዎች እና መንፈሳዊ መመሪያ በመስጠት ማገዝ ይችላሉ።

  > ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ስራዎቻቸውን ወንጌልን እንደሚያገለግሉበት መድረክ እንዲመለከቱ እንዴት ማበረታታት እንችላለን?

# ጾታዊ ማንነት

የኢትዮጵያ ሪፖርት

# እኛ ያገኘነው



በዲጂታል ጥናቱ ውስጥ የተሳተፉት አብዛኞቹ ወጣቶች ፆታ**ስንወለድ የምናገኘው እንደሆን ያምናሉ።**

**ከ5ቱ 1ዱ** ጥያቄው **ምን እንደሆነ እንዳልገባቸው**ተናግረዋል።





**8%** የሚሆኑት በጥናቱ ውስጥ የተሳተፉት ወጣቶች በቅርቡ **የግብረሰዶማዊነት እርኩሰት ፍላጎት እንደነበራቸው ተናግረዋል።**

**የግብረሰዶማዊነት እርኩሰት ፍላጎት** ከሴቶች ይልቅ **በወንዶች ላይ** ከፍ ይላል።





የ ጾታ ማንነት ግራ የመጋባት መጠን **ጥናት በተደረገባቸው በሁሉም ቡድኖች** ውስጥ ያለምንም ልዩነት **በጣም ዝቅተኛ ነው።**



በዚህ ትውልድ መካከል በፆታዊ ማንነትና በፆታ ግንኙነት ዙሪያ የሚደረግ ውይይት እየተለመደ መጥቷል። ከዚህም የተነሳ በጥናቱ የተሳተፉ ወጣቶች ምን ዓይነት አመለካከት እንዳላቸው ለማወቅ ፈልገን ጥያቄዎችን አቅርበንላቸዋል።

እንደዚህ አይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ በጣም ጥንቃቄ የሚያስፈልገው በመሆኑ ብሔራዊ ቡድኑ እነዚህን ጥያቄዎች በወረቀት ተጽፈው ለተሳታፊዎች ከተበተኑት የጥናቱ መጠይቆች መካከል ላለማካተት መርጧል። ይህ ክፍል በጣም አነስተኛ በቁጥር 53 ከሆኑ በዲጂታል በተወሰዱ ናሙናዎች ላይ የተመሠረተ ነው።

# ስለነዚህ ወጣቶች

## እድሜ

13-16 **15%**

17-20 **58%**

21-25 **26%**

**53** በጥናቱ የተሳተፉ ወጣቶች

## ሐይማኖት



ወንጌላውያን ክርስቲያን **70%**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ **28%**

ሌላ ሐይማኖት **1%**[1]

ወንዶች **40%**

ሴቶች **60%**

## አካባቢ

**77%** ከተማ (50,000 ወይም ከዚያ በላይ)

**11%** ከተማ ቀመስ (በ2,500 እና 50,000 መካከል)

**11%** ገጠር (ከ2,500 ያነሰ)

## መሰጠት

የተሰጠ ክርስቲያን **58%**

የስም ክርስቲያን **42%**

---

1 አንደኛው ወጣት ሌላ ሰው መርጧል። ምላሻቸው አድቬንቲስት የሚል ነበር። በዚህ ሪፖርት ላይ ከክርስቲያኖች ስለሚለዩ ከክርስቲያኖች ተነጥለው የተወሰዱ ሲሆን በጠቅላላው መዋዕቅራችን ውስጥ አልተካተቱም።

# ጾታዊ ማንነት

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሰጡ አብዛኞቹ ወጣቶች (70%) ፆታ በዋነኛነት የሚወሰነው ስንወለድ ይዘን በመጣነው እንደሆነ ይናገራሉ። ጥያቄ ከቀረበላቸው 5 ሰዎች መካከል አንዱ ጥያቄውን እንዳልተረዱት ተናገረዋል፤ ይህም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ጨርሶ ግንዛቤ እንደሌላቸው የሚጠቁም ይመስላል።

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶች ይልቅ በሰል ያሉ ወጣቶች ስለ ፆታ ያላቸው አመለካከት ባሕላዊ፣ ትራዲሽናል (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልከታ ማለት ነው) ከጥንት የነበረን አመለካከት ለመጠቆም ነው።

## ስለፆታ አመለካከት

ጾታ በዋነኝነት የተመሰረተው በ፡-




## ስለጾታ ያለ አመለካከት በእድሜ

ጾታ በዋነኛነት ስንወለድ ይዘን በተወለድነው ጾታዊ ማነነት ይወሰናል፡-




በተጨማሪም ወጣቶችን ስለ ፆታዊ ማንነታቸው የግል ልምዳቸውን ጠየቅናቸው። በጣም ጥቂት ቁጥር ያላቸው ወጣቶች በቅርቡ በፆታ ማንነታቸው ላይ ግራ መጋባት እንዳጋጠማቸው ወይም አንዳንድ ጊዜ ከራሳቸው በተቃራኒው ፆታ እንደሚሆነው ሲሆኑ ምቾት እንደሚሰማቸው ተናግረዋል። ያስታውሱ፣ እነዚህ ቁጥሮች በዲጂታል-ብቻ ናሙና ከተወሰደባቸው ጥቂት ቁጥሮች ላይ የተመሰረቱ ስለሆኑ፣ በዚህ ሪፖርት ውስጥ እንደተካተቱት እንደ ሌሎች መረጃዎች ሰፊውን ቁጥር የሚወክሉ አይደሉም።

በጣም ጥቂት ወጣቶች ሰዎች በአካላቸው ላይ ለውጥ አድርገው ጾታቸውን ቢቀይሩ ምንም ችግር የለውም ብለው ያምናሉ። ከ10 ሰዎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ጭራሽ ጥያቄውን እንዳልተረዱት ተናግረዋል።

## በፆታዊ ማንነት ግራ መጋባት

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ በፆታዊ ማንነትዎ የተነሳ ግራ መጋባት አጋጥምዎታል?




## የጾታ ፈተናዎቸ

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ፤ አሁን ካለዎት ጾታ ይልቅ በተቃራኒው ጾታ ቢሆኑ የበለጠ ራስዎትን መሆን እንደሚችሉ አስበው ያውቃሉ?




## ጾታ መቀየር

ሰዎች በአካላቸው ላይ ለውጥ አድርገው ጾታቸውን ቢቀይሩ ችግር አለው?[1]




# የተመሳሳይ ጾታ ወሲባዊ ፍላጎት

አሁን ላይ ያለው ትውልድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስንመለከተው የፆታ ስሜታቸውንና ወሲባዊ ፍላጎታቸውን በይበልጥ ለማወቅ በራሳቸው ማጥናት ላይ ትኩረት አድርገው ሲንቀሳቀሱ እንመለከታለን። በኢትዮጵያም በዚህ ጥናት ውስጥ በተሳተፉ ወጣቶች ላይ ይህንን ተመሳሳይ ነገር አይተናል። ከ10 ወጣቶች ውስጥ አንዱ ማለትም 8% የሚያኅለው በቅርቡ ተመሳሳይ ፆታ ባላቸው ሰዎች እንደተሳቡ ተናግረዋል።

ሴቶች በተመሳሳይ ጾታ የመሳብ እድላቸው ሰፊ ነው ከሚለው የ2020 አፍሪካ ጂ ዋይ ሲ ሪፖርት ጋር ሲነጻጸር በዚህኛው ጥናት ለተመሳሳይ ጾታ ስበት እንዳላቸው ሪፖርት ያደረጉት ወንዶች ከሴቶች ቁጥር በትንሹ ይበልጣል።[2] ተመሳሳይ ፆታ ባላቸው ሰዎች እንደሚሳቡ የተናገሩ ክርስቲያኖች ቢኖሩም ለእምነታቸው ጠንካራ መሰጠት ያላቸው ክርስቲያኖች ግን ብዙም እንደማያጋጥማቸው ተናግረዋል።

## የግብረሰዶማዊነት ፍላጎት

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ፣ ተመሳሳይ ጾታ ካለው ሰው ጋር የወሲብ ፍላጎት አድሮብኛል፡-




1 ከነጥብ በኋላ ያሉት ቁጥሮች በመጠጋጋታቸው ምክንያት ጠቅላላ ድምሩ ከ100% በላይ ይሆናል።
2 OneHope. (January 2021). Global Youth Culture, Africa Report. www.globalyouthculture.net, 57.

# ማጠቃለያ

የወጣቶች አስተያየት እየበሰሉ ሲሄዱ ሊቀየር ይችላል፤ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በዚህ ውስን ናሙና ላይ ስለ ፆታዊ ማንነት እና ወሲባዊ ስሜት በመሳሰሉት አስፈላጊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚያምኑትን ነገር በትንሹ ተመልክተናል። በተጨማሪም፣ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መመሪያ እና ምክር ለማግኘት የት እንደሚሄዱ አውቀናል (ተፅዕኖዎችን እና መሪ ድምፆችን የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)።

- **መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከቶችን ማጠናከር**
  በጥናቱ የተሳተፉት እነዚህ ወጣቶች በአብዛኛው በፆታዊ ማንነትና የወሲብ ስሜት ባሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ማወቅ የሚያጽናና ነገር ነው። ይሁን እንጂ ወጣቶች እያደጉና ሌሎች አስተያየቶችንና ድምፆችን መስማት ሲቀጥሉ አቋማቸውን እንዳይቀይሩ በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ማዳበር ያስፈልጋቸዋል።

  > ወጣቶች አምላክ የፆታ ስሜታቸውንና ግንኙነታቸውን በተመለከተ ያለውን እቅድ እንዲረዱና ይህን ዕቅድ እንዲቀበሉት እና እንዲወዱት እንዴት መርዳት እንችላለን?

- **ለከባድ ውይይቶች ይዘጋጁ**
  ወጣቶች በብዙ ተጽእኖዎች ለምሳሌ ሙዚቃ፣ መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የዲጂታል መድረኮች ላይ በሚቀርቡ እና የሕይወት አስፈላጊ ጥያቄዎች ላይ በሚሰጡ አመለካከቶች ይቀረጻሉ። ከላይ በተዘረዘሩት ተጽእኖዎች የሚመጡ ሃሳቦች እግዚአብሔር ለሕይወታችን ስላለው እቅድ መወያየትን ጨምሮ ትርጉም ያላቸው ውይይቶችን ለማድረግ እድል ይፈጥራሉ። እራሳችንን እና የሚቀጥለውን ትውልድ እንደ ፆታ ማንነት እና ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ የወሲብ ግንኙነትን የመሳሰሉ ፈታኝ ርዕሰ ጉዳዮችን በተመለከተ ግልጽና እውነትኛ ውይይት ለማድረግ ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔርን እውነት ግልጽ በሆነ መንገድና በፍቅር ለማካፈል እንዲሁም እርግጠኛ ያልሆኑ ወይም እርስ በርስ የሚጋጩ ስሜቶች የሚሰማቸውን ወጣቶች በትኩረት ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን ይኖርብናል።

  > አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶች እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ እምነታቸውን በሚያጠናክር መንገድ በተሻለ ሁኔታ መመርመር እንዲችሉ ማዘጋጀት የሚችሉት እንዴት ነው?

- **የቤተክርስቲያንን ተጽእኖ ማሳድግ**
  መጋቢዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት የሕይወትን ትርጉም መረዳት፣ ማወቅ እንዲሁም ማግኘት ይቻላል የሚሉ ጥያቄዎችን የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ መልስ መስጠት እንደሚችሉ እውቅና የተሰጣቸው ቢሆንም፣ ነገር ግን እንደ ፆታዊ ጉዳዮች እና ወሲብ ባሉ ሌሎች መሰረታዊ ውይይቶች ላይ እምብዛም አስተዋጾ ሲያደርጉ አይታይም። ወጣቶች በየዕለቱ ይበልጥ ውስብስብና ግራ የሚያጋባ እየሆነ በመጣ ዓለም ውስጥ ይኖራሉ፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደማይለወጥ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል፤ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ሰለእያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍሎች እንደሚናገር ሊያውቁ ያስፈልጋል።

  > ለዚህ ትውልድ ወጣቶች ቤተክርስቲያን በፆታዊ ጉዳዮች እና በወሲብ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመርመር በሚፈልጉ ጊዜ ሁሉ የሚሄዱባት አስተማማኝ ቦታ እንድትሆን ማድርግ እና ይህንንም ለወጣቶች ማሳወቅ የምንችለው እንዴት ነው?

# ስለ ዋንሆፕ

OneHope በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት፣ ሚኒስትሪዎች እና መንግስታት ጋር በመተባበር ከ2 ቢሊየን በላይ ህጻናትና ወጣቶች በእግዚአብሔር ቃል ደርሷል። OneHope በሀገር ውስጥ በሚደረግ ጥናት ላይ ተመስርቶ፣ ያዘጋጃቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናቶች ሁሉንም  እድሜና ባህል ባማከለ መልኩ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። OneHope እ.ኤ.አ ከ 1987 ዓ.ም ጀምሮ ልጆች የእግዚአብሔርን ታሪክ እንዲያውቁ ለመርዳት በሁሉም ሀገሮች ውስጥ ላሉ ልጆች እና ወጣቶች ሕይወትን የሚቀይር የተስፋ መልዕክት አጋርቷል። onehope.net

# ስለ ጥናቱ

ይህ ፕሮጀክት ከ13 እስከ 19 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን ከ20 በሚበልጡ አገሮች ላይ ጥናት ያካሄደ ዓለም አቀፍ የጥናት መርሐ ግብር አካል ነው። ዓለም አቀፉ ጥናት የተካሄደው እ.ኤ.አ ከየካቲት እስከ መጋቢት 2020 ዓ.ም. ነው። ይህ ጥናት ደግሞ እ.ኤ.አ ከሐምሌ እስከ ጥቅምት 2024 ባለው ጊዜ ውስጥ ተደርጓል።

መረጃው በመላ ኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎችን እና ክልሎችን የሚወክል ሲሆን ጥያቄዎችም ከሀገራዊ ይዘት ጋር እንዲስማሙ ተደርገዋል። አብዛኞቹ ወጣቶች በአካል በመቅረብ በጥናቱ የተሳተፉ ሲሆን መልሶቻቸውን በወረቀት (673 ከ726 ወይም ከ93%) ላይ አቅርበዋል። የወረቀት መጠይቁን በመሙላት ጥናቱ ላይ የተሳተፉ ወ ጣቶች ጥያቄዎችን መዝለል ይችሉ ነበር፤ ይሁን እንጂ ሪፖርቱ እንደሚያሳየው እያንዳንዱ ጥያቄ ቢያንስ በ698 ሰዎች ተመልሷል፤ ይህም ለጥናቱ የተፈለገውን ውክልና ሙሉ አሟልቶ ነበር። ጥቂት ቁጥር ያላቸው 53 ሰዎች መጠይቆቹን በዲጂታል በመሙላት በጥናቱ ተሳትፈዋል። በዲጂታል ጥናት ላይ ፆታዊ ስሜትን የተመለከቱ ጥቂት ተጨማሪ ጥያቄዎችን አካትቷል። እነዚህ ውጤቶች ፆታ ማንነትን በሚመለከተው የመጨረሻው ክፍል ውስጥ ለብቻቸው ተካትተዋል።

### ክርስቲያን

ራሳቸውን ወንጌላውያን፣ ኦርቶዶክስ ወይም ካቶሊክ ብለው የገለጹ ወጣቶች ሲካተቱ፣ ነገር ግን “ኢየሱስ ብቻ”፣ አድቬንቲስት ወይም ሐዋርያዊ ተብለው የገለጹት አልተካተቱም።

### የተሰጡ ክርስቲያኖች

ራሳቸውን ወንጌላውያን፣ ኦርቶዶክስ ወይም ካቶሊክ ብለው የገለጹ እና የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟሉ ወጣቶች፡-

- እግዚአብሔር እንዳለ እና በግል ከእርሱ ጋር ግኑኝነት ሊኖራቸው እንደሚችል ያምናሉ
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያምናሉ
- የኃጢአት ይቅርታ ሊገኝ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሆነ ያምናሉ
- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያምናሉ
- ቢያንስ በየሳምንቱ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳቸው ያነብባሉ
- በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ ይጸልያሉ

### የስም ክርስቲያኖች

ራሳቸውን ወንጌላውያን፣ ኦርቶዶክስ ወይም ካቶሊክ ብለው የገለጹ ነገር ግን ለተሰጡ ክርስቲያኖች የወጡትን የዋና እምነቶች ወይም ባህሪያት ወይንም መስፈርቶች ያላሟሉ ወጣቶች።

*Copyright © 2025 by OneHope, Inc.*
*OneHope (February 2025) Global Youth Culture, Ethiopia Report*
*www.globalyouthculture.net*

# GLOBAL
## YOUTH CULTURE

OneHope
God's Word. Every Child.